


የዓባ ምርት በደልጊ ቅ/ማርያም



# ትንሣኤ



በጎንደር ሀ ስብከት ጭልጋ አውራጃ አለፋ ጣቁሳ ወረዳ የደልጊ ማርያም ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፻፴፮

የሰኔና ሐምሌ ፲፱፻፹፩ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«የዚህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፥ ሥርዓትና ዜና ፥ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»

ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ኅሩያን ልሣነ ወርቅ በዛብህ
ም/ አዘጋጅ መ ክንፈ
ርግብ ማርቆስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

## አርእስት


ደብዳቤዎች ........ ፩
መሬቱን የሚያርስ እንጀራን ይጠግባል ........ ፪
ደብዳቤውን ማን ለወጠው ? ........ ፬
ዜና ሊቃውንት ........ ፯
ቸርነቱን ተናገሩ ........ ፯
የአለቃ ዓለሙ ማንደም አጭር የሕይወት ታሪክ ........ ፰
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፲
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ........ ፲፪
ከግራ ሕይወት ምን እንማራለን ........ ፲፬
በጎ አድራጊዋ ቤት ........ ፲፮
ዜና ዕረፍት ........ ፲፯
ጠ.ናችን ........ ፲፰
ሐዋርያው ናትናኤል ........ ፲፱
ይቅር በላቸው ብዬን ........ ፳፩
የናዘሬቱን መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን
ለመሥራት ኮሚቴ መቋቋሙ ተገለጸ ........ ፳፪
ልደታ ለማርያም ........ ፳፫


## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

መንፈሳዊ ሰላምታዬን በማስ ቀደም ለጥያቄየ አጥጋቢ መልስ እንደሚሰጠኝ በመተማመን ነው።

፩ኛ/ በአዲስ አበባ ከተማ በአን ዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ካህ ናቱ ሙሉ ሌሊት በሰዓታትና በማ ኅሌት ቁመው ሲያገለግሉ ያድሩና ቅዳሴ ሲገቡ ቁመው ማስቀደስ ሲገባቸው አንዳንድ ካህናትም ሆኑ መዘምራኑ ወጥተው ያለም ንም ሥራ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ሲዘዋወሩ ያረፍዳሉ ምዕመናኑ በፀጥታ ሲያስቀድሱ ካህናቱ ዕንቅ ፋት መሆናቸው ግራ የሚገባ ነው የአብያተ ክርስቲያናቱም አስተዳ ዳሪዎች አይቆጣጠሯቸው ለዚህ መፍትሔው ምንድን ነው?

፪ኛ/ ቃለ ዓዋዲ ባሁኑ ጊዜ የቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ሕግ መሆኑ የታወቀ ነው በውስ ጡም የሚገኘው ጽሑፍ የሰበካ ጉባኤ መዋጮ ክፍሎ የከፈለበትን መታወቂያ የያዘ ምእመን ለመ ንፈሳዊ አገልግሎት ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ቢጠይቅ በነፃ እንደሚያገኝ ይገልጻል ። ነገር ግን በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ቃለ ዓዋዲው የደነገገውን ሕግና የወሰነውን ውሳኔ ባለመቀበል የሰ በካ መዋጮ የከፈልከው ከሌላ ቦታ እንጂ ለእኛ አይደለም ስለ ዚህ ከዚያው ከከፈልክበት ደብር ጠይቅ እንጂ እኛ አገልግሎት ልን ሰጥህ አንችልም በማለት እያሰና በቱ ሕዝቡን ከቤተ ክርስቲያን ለማራቅ የሚሞክሩ አሉ ለዚህስ መፍትሔው ምንድን ነው?

፫ኛ/ በዜና ሊቃውንት ዓምድ የሚገለጸው ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሊቃውንት ናቸው? ወይስ በሕይወተ ሥጋ ያሉት ይገለጻሉ?

በሕይወት ያሉት ሊቃውንት የሚገለጹ ከሆነ በአዲስ አበባ እነ መልአከ ሰላም ምናሴ ዘለቀ እነ መምህር ታየ ደረሱ እነ መምህር ጌራ እነ መምህር ሐረገ ወይን ለምሳሌ ያህል እነዚህን ጠቀስኩ እንጂ ብዙ ሊቃውንት እንዳሉ የታወቀ ነው ታድያ እነዚህ ሊቃ ውንት ሁሉ በሊቃውንት ዓምድ ታሪካቸው እየወጣ ለአንባብያን ለምን አይቀርብም ።

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን ከበደ
አዲስ አበባ

<u>መልስ</u>

ቀኝ ጌታ ጥዑመ ልሳን ከበደ መንፈሳዊ ሰላምታዎን ስላቀረቡ ልን በቤተ ክርስቲያን ስም እናመ ሰግናለን ያቀረቧቸው ጥያቄዎች ፫ ሲሆኑ ፤

የአንደኛው ጥያቄ መልስ ቆመው በሰዓታትና በማኅሌት ሲደክሙ ካደሩ በኋላ በቅዳሴ ጊዜ ወጥቶ መሄድ ተገቢ አይደለም በሰዓታትና በማኅሌት ቁመው ጉሮ ሮዋቸው እስኪነቃ ድረስ አገልግ ለው ሲያበቁ በቅዳሴ ጊዜ ወጥተው መሄዳቸው ድካማቸው ያለማስሪያ ከመቅረቱም በላይ ሌሎችንም ይጐ ዳሉ ለምእመናን መልካም አር አያና አብነት በመሆን ፈንታ በቅ ዳሴ ጊዜ ወጥቶ መሄድ የመጥፎ አርአያ ምሳሌዎች መሆናቸው ነውና ።

ስለዚህ እንደኛ ራሳቸው መን ፈሳዊውን ክብር ከመቀበል ይር ቃሉ ፤ ምእመናንም እነሱን በማ የት ከማስቀደስና ቁሞ ከማገልገል ችላ ስለሚሉ ምዕራገ ጸሎት ከሆ ነው ቅዳሴ ማስቀደስ ይቀራሉ ፤ ይህ ራሳቸውንም ሌሎችንም ስለ ሚጐዳ ቁመው ካደሩ በኋላ ሳይ ወጡ በዚያው ቢያስቀድሱ መል ካም ነው ።

እነዚህ ሰዎች በቤተ ክርስቲ ያን ተቀጥረው የቤተ ክርስቲያ ንም ደመወዝ (ካላቸው) የሚከፈላ ቸው ከሆነ ግን የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ቢቆጣጠሩ መልካም ነው ። ምክንያቱም ከመጀመሪያ አገልግሎት እስከ ፍጻሜ ድረስ መቆየት ይኖርባቸዋልና እትው በሰላም ሳይባል ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ መሄድ በቤተ ክርስቲያን ሕግ የተከለከለ ነው ፤

፪ኛ/ አንድ የኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ በሰ በካ ጉባኤ ተመዝግቦ ወርኃዊ ክፍ ያውን የሚከፍልበት መታወቂያ ይዞ ከተገኘ ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ሄዶ የፈለገውን መንፈ ሳዊ አገልግሎት የመጠየቅ መብት አለው ፤ ግን የሰበካ ጉባዔ የከፈልክበት በእኛ ቤተ ክርስቲ ያን አይደለምና በከፈልክበት ደብር ጠይቅ እያሉ የሚያባርሩ ካህናት ካሉ ስሕተተኞች ናቸው ቤተ ክርስቲያናችን አንዲት ናት ሁለት አይደለችም ስለዚህ አንድ ምእመን የሚከፍለው የሰበካ ጉባኤ ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን እንደመሆኑ መጠን ከከፈልክበት ጠይቅ የከፈልከው ለእኛ አይደ ለም የሚለው አነጋገር በቤተ ክር ስቲያኑዋ መመሪያና ሕግ መሠ ረት የሚያስጠይቅ ነው ። ምክንያ ቱም በቅዱስ ሲኖዶስ የወጣው



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# "መሬቱን የሚያርስ እንጀራን ይጠግባል"

"ካልበሉ አሬሳ ካልለበሱ እንስሳ እንደሚባለው ለመኖር መብላት ለመብላት ደግሞ መሥራት አስፈላጊ መሆኑ የሚያጠያይቅ ትዳይ አይደለም ሕይወት ያለው ፍጡር ሁሉ ካልተመገበ ህላዊ ሊኖረው አይችልምና ።

የተራበ በልቶ እንደሚጠግብ ፡ የተጠማም ጠጥቶ እንደሚረካ ምድርም ዝናብን ከጠጣች በኋላ አካሏን ከይብስት ወደልምላሚ በመለወጥ የዘሩባትን ታበቅላለች የተከሉባትንም ታጸድቃለች የቀኑን ሐሩር የሌሊቱን ቁር ሳይፈራ ፡ በውርኃ ክረምት ከላይ የሚወርደውን ዝናብ ፡ ከታች ያለውን ጭቃ ሳይሰቀቅ ጠንክሮ በመሥራት ለደከመው ገበሬ የድካሙን ዋጋ ትክፍለዋለች በረከትን ግን የምትቀበለው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው ፡ ይህንን ባታደርግ ዘረ ቁርጥም ትባላለች መጨረሻዋም በእሳት መቃጠል ይሆናል ሲል ሐዋርያው ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ፮.፰ ተናግሯል ።

በሀገራችን በአንድ ዓመት ውስጥ አራት የተለያዩ ወቅቶች ይገኛሉ እነርሱም እንደሚከተለው ይከፈላሉ ።

፩ኛ. ከመስከረም ፳፮ እስከ ታኅሣሥ ፳፭ ቀን ያሉት ዕለታት ሲሆኑ ይህ ወቅት መፀው ተብሎ ተሠይሚል የአበባ ፡ የፍሬ የእሸት ወቅት ማለት ነው በክረምት ተዘርተው የበቀሉ ፡ አዝርዕት ተተክለው የጸደቁ አትክልት ፡ ፍሬያቸውን የሚሰጡት በዚሁ ወቅት ነው በዚህ ወቅት መሬት ሰማያዊ ኅብርን ታሳያለች ጋራው ሸንተረሩ በአበባና በፍሬ ተሸፍኖ ስለሚታይ ወጭ ወራጁ ኃላፊውና አግዳሚው ሁሉ በምድር ውበት ይማረካል ።

፪ኛ. ከታኅሣሥ ፳፮ እስከ መጋቢት ፳፭ ያለው ወርኃ ሐጋይ ይባላል ። በዚህ ወቅት መሬት የተለየ መልክን ይዛ ትታያለች አበቦችና ቅጠሎች ረግፈው ፡ ሣሩ ወደ ትቢያነት ተለውጦ የወንዝ ውሀዎች ኃይላቸው ተመናምኖ መሬት ከሣርና ከቅጠል ተራቁታ ለሐሩረ ፀሐይ ተጋልጣ የምትታይበት ወቅት ነው ።

፫ኛ. ከመጋቢት ፳፮ እስከ ሰኔ ፳፭ ቀን ያለው ወቅት ነው በደይ ይባላል የበልግ ዘመን ማለት ነው በዚህ ወቅት አንዳንድ ጊዜ መሬት በልምላሜ ተውባ ስትታይ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሐሩረ ፀሐይ በርትቶ ድርቁ ጸንቶ በእንሰሳት ላይም ሆነ በሰው ልዩ ልዩ ችግሮች ይደርሳሉ ። የመሬትም መልክ እንደተለበለበ ግንድ ሆኖ ይታያል ።

፬. ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ያለው ወቅት ነው ይህም ክረምት ይባላል አዝርዕት ተዘርተው በመብቀል የሚያድጉበት አትክልት ተተክለው የሚጸድቁበት አፍላጋት (ወንዞች) ኃይል አግኝተው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው የሚያሰሙበት መሬትም በልምላሜ ተውባ የአረንጓዴ መልክ የምታሳይበት ነው ።

በይበልጥ በወርኃ ክረምት ገበሬዎች ቀን በሥራ ተጠምደው ሲውሉ ሌሊት በሀሳብ ሲወጡ ሲወርዱ ማደሪቸው የሚካድ አይደለም አርሶ ቆፍሮ ወጥቶ ወርዶ ትልበትን አድክሞ ወዝን አንጠፍጥፎ መመገብ ተገቢ መሆኑን እግዚአብሔር አምላክ ሲያስረዳ አዳምን በአርዓያውና በምሳሌው ከፈጠረው በኋላ ወደ ገነት ወስዶ ሲያስቀምጠው እየሠራ እንዲበላ ነግሮታል ። ይኸውም "ሰውን ወስዶ ያበጃትና ይጠብቃት ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው በሚለው ቃል ይታወቃል ዘፍ.፪.፲፭ ።

ማነኛውም ሰው ሳይሠራ መብላት እንደማይገባው ቢታወቅም ሁሉም ሰው በአንድ ዓይነት የሥራ መስክ ተሰልፎ ለመሥራት አይችልም የእያንዳንዱ ሰው ስጦታ የተለያየ ሊሆን ይችላልና ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ሲገልጽ የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው አሠራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉንም በሁሉ አድሮ የሚያደርግ ግን አንድ እግዚአብሔር ነው ብሏል ፩ኛ ቆሮ ፲፪.፬ ፯

በተለይ በወርኃ ክረምት ምሬፋንና ቀንበሩን ከዘር ጋር በትከሻቸው ተሸክመው በሮችን በመንዳት



ወደእርሻቸው እየሔዱ ከላይ ዝናቡን ከታች ጭቃውን ሳይሰቀቁና ሳይፈሩ በሥራ የሚደክሙ ገበሬዎች ናቸው ።

እነርሱም የድካማቸውን ዋጋ አግኝተው ደስ የሚሰኙት በመከር ወራት ነው ። ሐዋርያው በጥቂቱ የሚዘራ በጥቂቱ ያጭዳል በበረከትም የሚዘራ በበረከት ያጭዳል "እንዳለው በክረምት ደክመኝ ታክተኝ ሰለቸኝ ሳይል ያለስንፍና አብዝቶ አርሶ ብዙ ዘርን የዘራ ገበሬ እጥፍ ድርብ የሆነ ምርትን እንደሚያመርት አይጠረጠርም ዝናቡን ብርዱን ጭቃውን በመፍራት በስንፍና ተውጦ የከረመ ገበሬ ግን በመከር ጊዜ የበይ ተመልካች ይሆናል ።

ነቢዩ ዳዊት "በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቀማሉ በሔዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ" ይላል መዝ ፻፳፭.፭ የረኃብ አጸፋው ጥጋብ ፡ እንደሆነ የኀዘንም አጸፋው ደስታ ነውና በወርኀ ክረምት ሳይሰንፉ ጠንክረው ያረሱና የዘሩ ገበሬዎች በመከር ጊዜ ድካማቸው ወደብርታት ረኃባቸው ወደ ጥጋብ ተለውጦላቸው እጅግ በጣም ደስ ይላቸዋል ።

ስለዚህ ምድሩን የሚያርስ እንጀራን ይጠግባል ተብሎ በመነሻው እንደተጠቀሰው ማንኛውም ገበሬ መሬቱን ጦም ሳያሳድር ጠንክሮ ያለ ስንፍና የማረስና የመቆፈር ግዴታ እንዳለበት ከልብ መገንዘብ ይኖርበታል ።

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፩ የዞረ)

በቃለ አዋዲ በገጽ 52 (ሀ) ላይ እንዲህ ይላል "በሰበካው ውስጥ ነዋሪ የሆነ በሰበካ ጉባኤ በአባልነት ታውቆ የተመዘገበና ሕጉን ያሟላ መታወቂያ የተሰጠው ምእመን ለምእመናን የሚገባውን አገልግሎት ማግኘት መብቱ ነው" ይላል ። በ(ለ) ፊደል የሚለውም" በዚህ ደንብ ውስጥ ከተገለጠው አስተዋጽኦ ሌላ ምእመናን ለካህናት ገንዘብ እንዲከፍሉ እያንዳንዱ ካህናትም ሊጠይቁ አይችሉም ።"

ሐ/ አንድ ምእመን በሰበካው ቤተ ክርስቲያን የሚገባውን ከከፈለ በተጨማሪ በሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዲከፍል አይገደድም ይላል ።"

የቃለ ዓዋዲው ደንብና ሥነ ሥርዓት ይህ ሆኖ ሳለ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚከለከሉ ካህናት ካሉ ግን ተሳስተዋልና ስሕተታቸውን እንዲያርሙ ቃለ ዓዋዲውንም እንዲያነቡ እናሳስባለን ።

፫ኛ/ ስለ ዜና ሊቃውንት ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩም ሆነ በሕይወተ ሥጋ ያሉት ታሪካቸው ይወጣል በሕወተ ሥጋ ያሉት የሊቃውንት ታሪክ የሚወጣ ከሆነ ለምን የእነ መልአከ ሰላም ምናሴና የሌሎችም አይወጣም ብለዋል ።

ሁሉም ይወጣል ለምሳሌ ከጠቀስዋቸው ሊቃውንት መካከል የመምህር ጌራ በመጽሔታችን ወጥቶና ታትሞ ተሰራጭተዋል ፡

ዜና ሊቃውንት በሚል ርእስ በትንሣኤ መጽሔት የሚታተመው ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩ ብቻ ሳይሆን በሕይወተ ሥጋ ስላሉም መምህራን ይታተማል ።

ለምሳሌ ፡ ታህሣሥ ወር 1979 ዓ.ም ቁጥር 109

ሰኔ ወር 1979 ዓ.ም ቁጥር 115

መስከረም ወር 1980 ዓ.ም ቁጥር 118

ቢመለከቱት ለመረዳት ይችላሉ አሁንም ቢሆን የሞቱትንም ሆነ በሕይወተ ሥጋ ያሉትን ታሪክ አዘጋጅቶ የሚልክልን ካገኘን እናወጣዋለን ።

እርስዎም በጥያቄው እንዲተባበሩን ሁሉ የሊቃውንቱን የሕይወት ታሪክ በመጻፍም እንደሚተባበሩን ተስፋ እናደርጋለን ።

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

በመጀመሪያ የክርስቶስ ፍቅር ከእናንተ ጋር ይሁን እላለሁ ከዚህም በማስከተል ጥያቄየን አቀርባለሁ ይኸውም ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ ዓርብ በተሰቀለበት ወቅት በአይሁድ ተይዞ በመስቀል እንደ ተሰቀለና ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ እንደ ለየ ይታወቃል ። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ጌታችን በመስቀል ላይ ራሱን ዘንበል አደረገ ይላል ጥያቄየም ከዚሁ ላይ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዘንበል ያደረገው ወደ ቀኝ ነው ወይስ ወደ ግራ ነው ይህንንም ለመጠየቅ ያስገደደኝ አንዳንድ ስዕሎችን ስመለከት ራሱን ወደ ግራ ሁኖ ሳየው በቤተ ክርስቲያናችን የተሳሉት ስዕሎች



www.ethiopianorthodox.org

# ደብዳቤውን ማን ለወጠው ?

የነበር እንዳልነበር ፡ ያዩት እንዳላዩት ፡ የሥሩት እንዳልሠሩት በመሆን ተለዋውጦ ስናገኘው እንዴት ሊሆን ቻለ ? በማለት መገረማችን አይቀርም ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል ከሆነ ሊሆን የማይችል ነገር እንደ

ማን ሁሉም ራሱን ወደ ቀኝ አዘን ብሎ ነው የማየው ስለዚህ ምሥጢሩ ስላልገባኝ አብራርታችሁ እንድታስረዱኝ መልሳችሁን እጠባበቃለሁ ።

ወ ሎ ሀ/ስብከት ደሴ ከተማ ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የሰ/ት/ቤት ተማሪ ታሪኩ አሰፋ ።

ተማሪ ታሪኩ አሰፋ ጥሩ ተመልክተሃል በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት ራሱን ወደ ቀኝ አዘንብሎ ነው የሚሳለው ይኸውም ታላቅ ምሥጢርን ያዘለ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰቀል በቀኝና በግራ ሁለት ወምበዴዎች ተሰቅለው ነበር ታድያ ከእነዚህ ከሁለቱ ወምበዴዎች አንዱ በቀኝ የተሰቀለው ጥጦስ ይባላል አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ሲለው ራሱን ወደ እሱ ዘንበል አድርጎ እውነት እልሃለሁ እንደ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ ብሎታል ። ስለዚህ ራሱን ያዘነበለው ወደ ቀኝ ነው በቀኝ ካለውም ወንምበዴ መነጋገሩን ለመረዳት የሉቃስ ወንጌልን ም.፳፫ቁ.፴፱ን ብትመለከት መልካም ነው ። ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያናችንን ስዕለ ስቅለት እንመልከተው ።

ከነፈርግብ ማርቆስ

ሌለ ከምናያቸውና ከምንሰማቸው ከታሪክም ከምንረዳቸው ነገሮች ማረጋገጥ እንችላለን ።

በርዕሱ ላይ በጥያቄ መልክ የተጠቀሰው ደብዳቤ ታሪክ እንደሚከተለው ነበር ። በቈስጠንጢኖስ ዘመን አብያተ ክርስቲያን እየተስፋፉ ሲሄዱ በእስክንድርያ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ቅዱስ ሚካኤልን የሚያምን አንድ ሰው ነበር። በየወሩ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል መታሰቢያ እያደረገ የተራቡትን ሲያበላ ፡ የተጠሙትን ሲያጠጣ ፡ የታረዙትን ሲያለብስና ደካሞችን ሲረዳ ይኖር ነበር። ይህንንም የማያደርግ አንድ ሀብታም ጐረቤቱ እየዘበተበትና ሊያጠቃው እየተሳለ ለብዙ ጊዜ አብረው ኖሩ ። ክርስቲያኑም ሰውዕለተ ሞቱ ሲደርስ ይህ የሚያደርገው ምግባረ ሠናይ ሁሉ እንዳይታጎል ለሚስቱ ተናገሮ ሞተ ።

ሚስቱም በዓሉን ስታከብር ዝክሩን ስትዘክር ሳለ ባሏ ከመሞቱ በፊት አርግዛ ስለነበር የመውለጃዋ ቀን ደርሶ ምጥ ያዛት ። ሲጠናባትም የቅዱስ ሚካኤልን ስም በመጥራት ድምጽዋን ስታሰማ ቤትዋ በብርሃን ተሞልቶ አይዞሽ አትጨነቂ ፡ ደስ ይበልሽ የምትወልጅው ልጅ ታላቅ ሰው ይሆናል ። የዚህንም ባለፀጋ ሀብት ይወርሳል ብሎ ነግሯት ተሠውሮ አል ። ወዲያውም በሰላም ወንድ ልጅ ተገላገላለች ።

ባለፀጋውም ይህን ቃል ይሰማ ነበርና ልጁ አድጎ አሥር ዓመት ሲሞላው "ይህን ልጅ ስጭኝ እያበላሁ ፡ እያጠጣሁ ፡ እያለበስሁ ፡ ልያዘው እሱም ያልፍለታል ለአንቺም ገንዘብ እሰጥሻለሁ" አላት እናቱ ለጊዜው ችግሯት ስለነበር እንደ ልጅ አድርጎ ያሳድገዋል ኋላም ሀብቱን ያወርሰዋል በማለት ሰጠችው ባለፀጋውም ልጁን ተቀብሎ በቁመቱ ልክ ሣጥን አሠርቶ በውስጡ አስገብቶ በመቆለፍ ከባሕር ላይ ጣለው ሣጥኑም ብዙ አገር አቋርጦ ከሄደ በኋላ አንድ የበግ እረኛ አግኝቶ ወደ ቤቱ ወሰዶ ሣጥኑን ቢከፍተው ወጣቱን ከነሕይወቱ አግኝቶታል ስሙንም ከባሕር የተገኘ ሲል "ባሕራን" ብሎ በመጥራት በቤቱ እያገለገለ እንዲኖር አድርጓል ። ከብዙ ጊዜም በኋላ ወደ ባሕር የጣለው ሀብታም ለንግድ ወደዚህ አገር መጥቶ በዚህ ቤት በእንግድነት አደረ ። ልጁንም ባሕራን እያሉ ሲጠሩት ሰምቶ ለምን ባሕራን እንዳሉት ቢጠይቃቸው ከባሕር ያገኙት መሆኑንና ታሪኩን አንድ በአንድ ይነግሩታል ።

ሀብታሙም እሱ የጣለው መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ለአሳዳጊው "ይህ ልጅ በቤቴ ረስቸው የመጣሁት ነገር አለና ደብዳቤ ያድርስልኝ" በማለት ገንዘብ ሰጥቶ ይለምነዋል ። ደብዳቤውም" ይህን ደብዳቤ ይዞ የሚመጣው ልጅ ቀድሞ ወደባሕር ጥየው የነበረው ነውና እንደደረሰ ሰው ሳያይ ገድላችሁ ቅበሩት" የሚል ነበር ።

ባሕራንም ይህን ደብዳቤ ይዞ ወደ ሀብታሙ ቤት ሲጓዝ በመንገድ ላይ ቅዱስ ሚካኤል መንገደኛ በመምሰል በፈረስ ላይ ሆኖ ሰላምታ ከሰጠው በኋላ "ከየት መጣህ? የት ትሄዳለህ? የያዝከውስ ምንድነው? ብሎ ጠየቀው ወጣቱም ታማኝ ስለነበረ ደብዳቤውን ከተላከለት ሰው ሌላ ለማሳየት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ቅዱስ ሚካኤል "በሩቅ ብቻ አሳየኝ" ብሎ ደብዳቤውን ብቅ አድርጎ አሳየው ቅዱስ ሚካኤል ደብዳቤውን እፍ በማለት ለውጦታል ። ባሕራንም ወደ ሀብታሙ ቤት እንደደረሰ ደብዳቤውን ሰጥቶ ሲነበብ እኔ በዚሁ የምዘገይ ስለሆነ ይህ ልጅ እንደደረሰ በቤቱም በውጭም ያለውን ሀብቴን በሙሉ አውርሳችሁ ልጄን ድራችሁለት እንድትቆዩኝ" የሚል ሆኖ ተገኘ ። በዚህም መሠረት ሀብቱን አውርሰውት ልጁንም ድረውለት ሲደሰቱ ይሰነብታሉ ፡

ሀብታሙም ከብዙ ቀን በኋላ ወደ ሀገሩ ተመልሶ በቤቱ አቅራቢያ ሲደርስ አንዱን አገልጋዩን በውጭ አግኝቶ "ይህ የምሰማው ሁካታ ምንድነው ? ብሎ ቢጠይቀው ይህማ ደብዳቤ ጽፈህ በማህተም አረጋግጠህ ባዘዝከው መሠረት በውጭ ያለ ሀብትህን ፡ በቤት ያለ ንብረትህን ሁሉ ለባሕራን አውርሰነው ፡ ልጅህንም ድረን ለት ዘመድ አዝማድ ጐረቤት ፡ ባእድ ሳይቀር ተጠርቶ ዓርባ ቀን ሙሉ እየበላ እየጠጣ እየዘፈነና እየተደሰተ ነው አለው ። በዚህ ጊዜ ከፈረሱ ላይ በድንጋጤ ወድቆ እንደሞተና ባሕርንም እንደተነገረለት ሀብቱን ወርሶ የቅዱስ ሚካኤልን መታሰቢያ እያደረገ በእምነቱ ጸንቶ እንደኖረ ታሪኩ በሰፊው ያብራራል ።" የግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል ። መዝ. ፴፫.፯።

ቅዱስ ሚካኤል ለወደጆቹና ለወደዳቸው ያደረገው ተራድኦ በእጭሩ ተዘርዝሮ አያልቅም ብዙውን ጊዜ ለምሕረት ከእግዚአብሔር እየተላከ ሰውን ከበሽታ ከረኃብ ፡ ከስደት ፡ ከሞት ፡ ከጦርነትና ከልዩ ልዩ አደጋ የሚያድን ተራዳኢ መልአክ ነው ። እሥራኤል ከግብፅ ሲወጡ በመንገድ ላይ ያደረገላቸው እርዳታ ይስሐቅን ከመሠዋት አድኖ በምትኩ የተላከለትን በግ እንዳቀረበለት ሕዝቅያስን ከሰናክሬምና ከሠራዊቱ እንዳደነውና የመሳሰለውን ከቅዱሳት መጻሕፍት ስንመለከት ምን ያህል የደቅርታ መልአክ መሆኑን እንረዳለን ። ዘፍጥ.፳፪. ፲፩ መዝ ፺.፲፩—፲፪፡ ፪ኛ ነገ፡ ፲፱ —፴፭ ።

እንዲሁም ቅድስት አፎምያ ባሏ አስተራኒቆስ ከሞተባት በኋላ በጾምና በጸሎት ተወስና ከምትኖርበት ጋኔን በተለያየ መንገድ ሊያሳስታት ቢሞክር በሚካኤል ስም ድል እንዳደረገችው በዚሁ ወርድርሳኑ ላይ ተብራርቷል ።

የሀብታሙንም ሰው ተግባር ስንመለከት ባደረበት ሰይጣናዊ ሀሳብ የክርስቲያን ጐረቤቶቹን ሃይማኖት እያንኳሰሰ ምግባራቸውን እየነቀፈ ከመኖሩም በላይ ባሕራንን ለመግደል በፈጸመው በደል እራሱ ሊጠፋ ቻለ ። መጀመሪያ ባሕራን በተወለደበት ቀን መልአኩ ወርዶ ሀብቱን እንደሚወርስ ትንቢት ሲናገርበት ፡ ዳግመኛም ልጁን አታልሎ በመውሰድ ወደባሕር ከጣለው በኋላ መልአኩ ጠብቆት ባላሰበው ቦታ ከነሕይወቱ ሲያገኘው በመፍራትና በመጸጸት ፋንታ እንደገና ጠማረ ሞቱን (የሞቱን ደብዳቤ) አስይዞ ወደሞት ላከው ስለዚህ ምንም እንኳ እምነት ባይኖረው በተደጋጋሚ የሠራሁት ክፉ ሥራ ያጠፋኛል ብሎ ሳያስብ በመቅረቱ እራሱ ላይ የሞት ፍርድ አስከተለ ።

ሰው መልካም ሥራው እንደሚያለማውና ክፉ ሥራው እንደሚያጠፋው ያውቃል ነገር ግን በላዩ ላይ ያለው ክፉ መንፈስ እየገፋፋ ለጥፋት ሲዳርገው ይኖራል ። ይህም እራስን በመውደድ ፡ ለጥቅምና ለገንዘብ በመገዛት የሚመጣ ነው በፍጹም እምነትና በፈሪሃ እግዚአብሔር ከሆነ ግን የመጣውና የተቃጣው ጥፋት ሁሉ እንደማያገኘው ከዚህ ታሪክ መማር ይቻላል ። እንግዲህ እኛም በእምነት ጸንተን በንስሐ እየታደስን ፡ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል በማክበር በስሙም ለተራበ አብልተን ለጠማ አጠጥተን ለታረዘ አልብሰን መኖር ይገባናል ። ይህንን ካደረግን በየቀኑ የሚመዘገበው የበደል ደብዳቤ ሁሉ መልአክ ሚካኤል በተሰጠው ሥልጣን ወደ ሕይወት ለውጦ በሕይወት ሳለን እንደሚጠብቀን በወዲያኛው ዓለምም ሀብተ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያወርሰን አንጠራጠርም ።

መ መንክር ዋሴ





www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## ፴፰ ዓመታት ያስተማሩ

በዛሬው ጽሑፋችን ለአንባብያን የምናቀርበው በማስተማር ተግባር ላይ ከሚገኙት የአብነት መምህራን የመምህር ይሄይስ ካሣን የሕይወት ታሪክ በአጭሩ ነው ።

መምህር ይሄይስ ካሣ በጐጃም ሀ/ ስብከት በብቸና አውራጃ



መምህር ይሄይስ በቅኔ ዘረፋ ላይ እንዳሉ

በ፲፱፻፲፱ ዓ/ም ከአባታቸው አቶ ካሣ ራድ ከእናታቸው ከወ/ሮ እህትነሽ አደገ ተወለዱ ፡ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ከአባ ገብረ ጊዮርጊስ ፊደል ቆጥረው ዳዊት ደግመዋል ።

ከዚህም ቀጥለው ወደ እነከር ቅዱስ ጊዮርጊስ ሄደው ከመሪጌታ አይለኝ ትርፌ ከተባሉ መምህር ጾመ ድጓና የቃል ትምህርት የዘወትር ምዕራፍ በሚገባ ከተማሩ በኋላ በገና ሚካኤል ወደሚባለው ደብር በመሄድ ከመሪጌታ ጥበቡ ቅኔ ተምረዋል ። ቀጥሎም ወደ ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ተመልሰው ከየኔታ ውብሸት ቀደም ሲል የተማሩትን ቅኔ በመክለስ አገባቡንና እርባ ቅምሩን ተምረው በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ። ከእኒሁ መምህር መጽሐፈ ነገሥት የዳዊት ፡ የውዳሴ ማርያም የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ተምረዋል ።

መምህር ይሄይስ የመማር ፍላጐታቸው ገና ያላከተመ በመሆኑ ቅኔ እያስተማሩ የረገ ቅዱስ ሚካኤል ከነበሩት መሪጌታ ታሪኩ አቋቋም ተምረዋል ፡ ከዚያ በኋላ ቀቸር ሚካኤል በተባለው ደብር ማስተማራቸውን ቀጥለዋል ፡ ማስተማርም የጀመሩት በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም ነው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከእርሳቸው ቅኔ እያስተማሩ ከማስነገርና ከመዝረፍ እንዲሁም ከማስተማር ደረጃ የደረሱ መቶ አምሳ በላይ መሆናቸውን መሪጌታ ይሄይስ ገልጸውልናል ።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ ከእርሳቸው ከተማሩት ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው የሚያስተምሩት ፴ መምህራንን ቆጥረው ነገረውናል መምህር ይሄይስ ዓይነ ሥውር ሲሆኑ የሚኖሩት በድንግልና ነው በ፲፱፻፶፱ ዓ ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም ሄደው መንኩሰው የማስተማር ተግባራቸውን ቀጥለዋል ከላይ እንደተጠቀሰው ማስተማር የጀመሩት በ፲፱፻፵፫ ዓ ም ስለሆነ ፴፰ ዓመት አስተምረዋል ማለት ነው ።

ያስተማሩትም ያለዋጋ የተማሯቸውትን ዋጋ ሳትቀበሉ አስተምሩት ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባዘዘው መሠረት ያለ ደመወዝ በነፃ ነው ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ለአብነት መምህራን እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በወር ብር ፸ ይሰጣቸዋል እንዲሁም ለ፲ ተማሪዎች በወር ፳ ብር እየተከፈላቸው የሚማሩ መሆናቸውን መምህር ይሄይስ ካሣ ገልጸውልናል ። በተጨማሪም ደመወዝ ሳይኖራቸው እየለመኑ እየበሉ ከሚማሩት ተማሪዎች ይልቅ ደመወዝ ያላቸውን በጥብቅ እየተቆጣጠሩ እንደሚያስተምሯቸው ተናግረዋል ከቅኔው ጋር ነገሥት የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜ ያስተምራሉ ።

መምህር ይሄይስ ካሣ ወደፊት ስለአላቸው ዓለማ ጠይቀናቸው ሲያብራሩ የእኔ ዓላማ ያው ማስተማር ብቻ ነው እግዚአብሔር በዚህ ዓለም እንድኖር እስከፈቀደልኝ ዘመን ድረስ በትጋትና በንቃት ከማስተማር ወደ ኋላ አልልም ። ነገር ግን ሳላስታውስ



አባ መ ይሄይስ እኒህ ናቸው

የማላልፈው ቀለብ ስለሌላቸው ተማሮች ነው ።

የምግብ የልብስና የጤና ችግሮች ስለአሉ እነዚህ የሚቃለሉበት ዘዴ በእናንተ በኩል ይገኝ እንደሆነ ብትፈልጉልን በማለት መምህር ይሄይስ አሳባቸውን አጠቃለዋል ፡ እኛም ችግሩን ለማቃለል ሚችለው በሀ ስብከቱ በአውራጃዎች ፡ በወረዳዎችና ፡ በየአንዳንዱ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰበካ ጉባኤ ሲጠናከር መሆኑን በመግለጽ የያዙትን ጉባኤ በማጠናከር ቤተ ክርስቲያንን እያገለገሉ በእግራቸው የሚተኩ ሊቃውንትን አስመስለው አሳክ

ለው እንዲያወጡ አደራ ብለናቸዋል ።

በተጨማሪም የሀ ስብከቱ ሰበካ ጉባኤ እየለመኑ ለሚበሉ ተማሮች የልብስ እርዳታ ከዓመት አንድ ጊዜ እንኳን ቢያደርግላቸው ተማሮች ያለችግር ትምህርታቸውን ለመከታተል እንደሚችሉ አያጠራጥርም ።

# ቸርነቱን ተናገሩ

ዘመን የማይሽረው ተወዳዳሪ የሌለው ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ ቸር እንደማይገኝ ነቢዩ ዳዊት እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቀምሳችሁ እወቁ ሲል የተናገረው ቃል ታላቅ እማኝ ሆኖ ይመሰክርልናል።

ይህ ከሆነ እግዚአብሔር ቸር ነው የሚለው የእማኝነት ቃል ትርጉሙ ምን እንደሆነ ገብቶናል ማለት ነው ። የቸርነቱና የብልጽግናው ተካፋይ መሆናችንን ከተረዳን ግን ማስተዋል አያዳግተንም ለምሳሌ በዙሪያችን ብንመለከት እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን በየቀኑ የሚሰጠን የጸጋው የቸርነቱ ልግስና በፊታችን ይቀርብልናል ።

የዐሐይ የጨረቃ እንዲሁም የከዋክብት ብርሃን በጠፈር ላይ ስለተዘረጋ በሙቀቱም በብርሃኑም እንጠቀምበታለን እንዲሁም በምድር ላይ በዝናም እየበቀለ የሚገኘው ቅጠላቅጠል ሳርና እህል ሌላም ስርዶ የሚበቅል ነገር ሁሉ ከአምላካችን ከብልጽግናው ሙላት ለጥቅማችን የተፈጠረ የቸርነት ስጦታ ነው ። ከዚህም የተነሣ የዐሐይ ሙቀት ባይኖር ኖሮ ዓለማችን የበረዶ ዓለም ስለምትሆን ሰው ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ተንቀሳቃሽም ሆነ የማይንቀሳቀስ ፍጥረት ሁሉ በቅዝቃዜው ስለሚጠቃ ሊኖሩ ባልቻለም ነበር ።

ዝናምም ባይኖር ኖሮ ለሰውም ሆነ ለእንስሳ የሚያገለግሉት አዝዕርትና ተክሎች ለመጠጥም ሆነ ለንጽህና የሚጠቅመው ውኃ ስለማይገኝ የጠቅላላው የፍጥረት ኑሮ ባቋረጠ ነበር ። እንዲሁም አየር ባይኖር ኖሮ ሰው የሚተነፍሰውና የሚቀበለው ተለዋጭ አዲስ አየር ባለማግኘቱ ህይወት አይኖረውም ነበር ። እነዚህ ሁሉ ከእግዚአብሔር ቸርነት ለሰው የሚሰጡ በረከቶች በመሆናቸው ሰዎች ስንባል ያለ እግዚአብሔር ዕርዳታ ልንኖር እንደማንችልና ከቸርነቱም ሙላት ተካፋዮች ካልሆን እንደምንደኸይ እነዚህ እማኞች ናቸው

ስለዚህም ወንጌላዊው የእግዚአብሔርን ቸርነትና ብልጽግና ሲገልጽ እርሱ በክፉዎችና በበጐዎችም ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጠአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባል ብሏል ማቴዎስ ምዕ ፭ ቁ ፵፭

እርግጥም እግዚአብሔር ቸር እንደመሆኑ መጠን ልደጐች ብቻ ሳይሆን ለክፉዎችም የፀሐይ ብርሃንና ሙቀት በትክክል ያድላል ። ለጻድቃንም ብቻ ሳይሆን ለኃጥአንም ጭምር የምህረት ዝናም ያዘንማል አዲስ አየርንም እየለዋወጠ ይሰጣል የሰው ልጅ ግን እነዚህን በጥበቡና በዕውቀቱ ቢፈላሰፍባቸውና በራሱም ፈጠራ ቢያስገኛ





www.ethiopianorthodox.org

ቻው ኖሮ እንደ ኤሌትሪክ ብርሃን የፀሐይ ብርሃንና ሙቀትን በአንጉል ውስጥ አግብቶ ዝናምንም በቧንቧ ይዞ የሚተነፍሰውንም አዲስ አየር መስታወት በመሰለ ነገር አፍና ገንዘብ ላላቸውና መክፈል ለሚችሉ ብቻ ያድል ነበር ። መክፈል የማይችሉ ድሆች ግን ከፀሐይ ሙቀትና ብርሃን ጠልም ከሚሰጠው ዝናም ሀይወትም ከሚሰጠው ካየር በጠቅላላው እኒህንና እነዚህን ከመሳሰሉ ነገሮች ተለይተው በቀሩ ነበር ። ከማንኛውም ባለጸጋ ይልቅ እግዚአብሔርን ታላቅ ቸር ሲያሰኘው የሚኖረው እነዚህን እና ሌሎቹንም ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ያለ ገንዘብ በነፃ ለሁሉም በማደሉ ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስም ሁሉ ለኛ ከእግዚአብሔር እንደተሰጠንና ሁሉ ነገር ለኛ እንደሆነ ሲመሰክር ዓለምም ቢሆን ህይወትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን ሁሉ የእናንተ ነው እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ብሎ አል አንደኛ ቆሮ·ምዕ·፫ ቁ·፳፪ ። እንደሐዋርያውም አነጋገር እግዚ ብሔር ለፍጥረቱ የለገሰው ስጦታ ምንም ነገር የማይጐድለው ፍጹም በመሆኑ ሁሉ የኛ ነው ። የኛም ያልሆነ ምንም ነገር የለም ። ስለዚህ ከሁሉም በላይ አንድን በት ዘንድ አንድ ልጁን ስጠን ከልጁም ጋር ሁሉን ነገር አደለን ስለዚህ ሁሉ የእናንተ ነው እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ይለናል ይህም የእግዚአብሔር ቸርነት ወሰን የሌለው መሆኑን የሚገልጽ ልን ቃል ነው በዚህ አኳኋን ምዕመናን የሆን ሁሉ ከክርስቶስ ክፍል አለን ማለት ነው በእርሱ አማካይነት ሁሉ ነገር ተሰጥቶ ናል ይህ ቃል የያዘውን የመንፈስ ብልጽግና ከልብ የተቀበልን እንደ ሆነ ከድህነትና ከመንፈስ ጭንቀት እንገላገላለን ። ከእግዚአብሔርም ልግስና ሥር ስለምንሆን አን ዳች ነገር አይጐድልብንም ። እር ግጥ ነው እግዚአብሔር ለኛ ያልሰጠን ነገር የለም ሁሉን ነገር ሰጥቶ ናል ሆኖም እራሳችን ብቻ እየተ ጠቀምን ለሌላው ሳንሰጥ ለራሳ ችን ብቻ ይብቃን እንድናስቀረው አያስፈልግም ከርሱ ያገኘነውን ከርሱም የተቀበልነውን እንደገና ለርሱ መልስን እንድንሰጠው ያሻል እግዚአብሔር የኔ የሆነ ማን ኛው ነገር የእናንተ ነው ብሎናል እኛስ አምላካችንን የእኛ የሆነው ሁሉ የአንተ ነው ለማለት እናስባ ለን?

የእግዚአብሔር ብልጽግና ወሰን የሌለው መሆኑን የተረዳው ቅዱስ ጴጥሮስም እርሱ ስለ እና ንተ ያሳባልና የሚያስጨንቃች ሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት ብሏል አንደኛ ጴጥሮስ ምዕ· ፭·፯·፯ እንዳለውም ክርስቲያን የሆን ሁሉ የእግዚአብሔርን ብል ጽግና እስኪታደልን ድረስ በጸ ሎት ከመጠባበቅ በቀር በችግር መልክ እየታየን የክርስቶስን ስምና ክብር ጭምር ማስወቀስና መስደብ የለብንም ።

ይሁን እንጂ ችግራችንን በአም ላክ ላይ መጣል ያስፈልገናል ። ምክንያቱም ችግራችንን በሱ ላይ እየሦራን ከጣልን የደኸዩትን ሁሉ ስለሚያበለጽግ እኛንም የመ ንፈስ ባለጸጎች ያደርገናል ። በፍ ቅርም የበለጸገ ከመሆኑ ባይ የሆ ነው ህይወታችን በፍቅሩ ይሞላ ዋል እግዚአብሔር የምህረትም ባለጸጋ በመሆኑ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ስለሚለን ቸርነቱን መናገር ይገባናል ። እርሱ የሠራ ውንም የነገውንም ፍላጐታችንን ያሚላልናል ለአምላካችን የሚሳነ ውና የሚጐድለው ነገር ስለሌለ ለምንጠራው ሁሉ ቅርብ ነው ። ለእኛ የሚያስፈልገን ግን በእውነ ተኛ ልብ እርሱን መጥራት ብቻ ነው ። እርሱም የሚጐድለንን ማንኛውንም ነገር ሁሉ ስለሚያ ሚላልን የሥጋም የነፍስም ባለጠ ጐች እንሆናለን ለምኑ ይሰጣች ኋል ተብሏልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



## የአለቃ ዓለሙ ወንድም

# አጭር የሕይወት ታሪክ

አለቃ ዓለሙ ወንድም በጎንደር ክ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ከአባታቸው ከቄስ ወንድም ጎ ሚካኤልና ከእናታቸው ከወ ሮ ጎጥረቴ ወንድም ሰኔ ፲፫ ቀን ፲፱፻ ዓ ም ተወለዱ ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደ ረስ እዚያው በተወለዱበት ደብር መካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ ቤተ ክርስቲያን ከአባታቸው ከቄስ ወንድም ጎ ሚካኤል የን ባብ የዳዊት የውዳሴ ማርያምና የመልክ መልክ ትምህርታቸውን አጠናቀው የዲቁና ማዕረግ ከብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ተቀብለዋል ። ከዚያም በጎንደር ክ ሀገር እስቴ ወረዳ ማኅደረ ማርያም ተብላ በም ትጠራው ታሪካዊት ደብር ከታወቂት የቅኔ መምህር ከመምህር መንገሻ ቅኔን ከነአገባቡና እንዲሁም ጸዋትወ ዜማን ምእራፍን ጾመ ድጓንና ድጓን በሚገባ አጠናቀው ተምረው እዚያው ጎንደር ውስጥ አረቢያ መድኃኔ ዓለም ከመምህር አሰናቀው የአቋቋም ትምህርት ከተማሩ በኋላ ጎንደር ከተማ በመሄድ በዐታ ከሚገኙት ከቀድሞው የአቋቋም መምህር ከየ



አለቃ ዓለሙ ወንድም እኒህ ነበሩ

ኔታ ክፍሌ በመምህርነት ተመርቀዋል ።

ከዚህም በኋላ በጊዜው በታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት መታወቅ የሚገባውን የቁም ጽሑፍ ለመማር ወደተወለዱበት መካነ ሰማዕት ቅዱስ ገላውዴዎስ ተመልሰው በአባታቸው አማካይነት የቁም ጽሕፈት ትምህርት ተምረዋል ።

አለቃ ዓለሙ ወንድም መንፈሳዊ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም ወደ ዋናው ከተማ ጎንደር በመሄድ በጎንደር ከተማ በሚገኘው በደብረ ብርሃን ሥላሴ በመሪጌትነት ሲያገለግሉ ቆይተው በዘመኑ በጎንደር ቤተ መንግሥት ነዋሪ በነበሩት በራስ ጉግሳ ወሌ ፈቃድ የታሪክ ጸሐፊ በመሆን በርከት ያሉ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ መጻሕፍትን ቆዳ በመፋቅ ብራና በማዘጋጀት ብርዕ በመቅረጽና ቀለም በመበጥበጥ ለሰባት ዓመታት ያህል በቤተ መንግሥቱ ውስጥ ብዙ ታሪክ ያላቸውና ቅርስ ሊሆኑ የሚችሉ መጻሕፍትን ጽፈዋል ።

አለቃ ዓለሙ ወንድም በዚህ ታላቅ ሙያቸው በተለያየ ጊዜ በጊዜው ከነበሩት ከታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎችና የገዳማት አለቆች ጥንግ ድርብ ቀፍጣን ቀሚስና ካባ ተሸልመዋል ። በ፲፱፻፳፰ ዓ/ም በደብረ ታቦር አውራጃ ግንድ አጠመም ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ እንዲሆኑ ሹመት ተሰጥቷቸው ይህንኑ ደብር ለስምንት ዓመታት ያህል በቅንነት አገልግለዋል።

አለቃ ዓለሙ ወንድም በ፲፱፻፴፯ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተ ክርስቲያን ለጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ፈቃድ ወደ አዲስ አበባ መካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን መጥተው ተሰጥኦቸው በሆነው የቁም ጽሕፈት ሙያ ድርሳነ ሚካኤልን በብራና እንዲጽፉ ተጠይቀው የቁም ጽሕፈት ሙያቸውን በሚገባ የሚያስመሰክርና የታሪክ ቅርስ የሚሆን ጽሑፍ ጽፈው ለብፁዕነታቸው አስረክበዋል ። በዚሁ ጊዜ የጻፏቸው መልክአ ኢየሉጣ ፡ የዓመት ዘቅና የማቴዎስ ወንጌል ታሪክን ለማስታወስ ባገለገሉበት በመካነ ሰማዕት ቅ/ቂርቆስ ደብር ለመሪጌትነት ተቀምጠው ይገኛሉ ። ከዚህ በኋላ ነው በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም በጥቅምት ወር ለሠላሣ አመታት ያህል በተ ክለኝነት ባገለገሉበትና ስብሐተ እግዚአብሔርን እንደምንጭ ያፈልቁበት ከነበረበት አዲስ አበባ መካነ ሰማዕት ቅ/ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን በመሪጌትነት የተቀጠሩት በዚህም ደብር በነበሩበት ጊዜ በልዩ ልዩ አድባራትና ገዳ ማት እንዲሁም በክብረ በዓል ቀን ደብሩን በመወከልም ሆነ በመመ ረጥ በማናቸውም የቤተ ክርስቲ ያን አገልግሎት በመሳተፍ ከፍ ተኛ ግልጋሎት ከመስጠታቸው የተነሳ ከቤተ መንግሥት በሙያ ቸው የክብር ልብስና ካባ ተሸል መዋል።

አለቃ ዓለሙ ወንድም በእውነ ተኛ አገልግሎታቸውና በተወዳጅ ጠባያቸው ከቤተ ክርስቲያን ተመ ርጠው በፍርድ ቤት ጸሐፊነትና ዳኝነት በአርሲ ፡ በሲዳሞና በሸዋ ክ/ሀገራት ለብዙ ጊዜያት በቅንነ ትና በታማኝነት አገልግለው በጡ ረታ የተገለሉ ናቸው ። ከ፲፱፻፶፫ ዓ/ም ጀምሮ በህመም ምክንያት መሥራት እስካቃታቸው እስከ ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ታቦቱ ከተተከለ ጀምሮ የጫንጮ ማህደረ መለኮት ቅዱስ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ በመሆን ለአሥራ አምስት ዓመታት ያህል በቅን ሲያገለግሉ ቆይተዋል ።

አለቃ ዓለሙ ወንድም ከህፃን ነት ዘመናቸው ጀምሮ ሙሉ እድ ሜያቸውን ቤተ ክርስቲያንን በቅን ያገለግሉ ነበሩ ። ሆኖም ፍጡር ናቸውና "አ አዳም መሬት አንተ ወትገብእ ውስተ መሬት" ያለው ቃል ይፈጸም ዘንድ ከሚወዷቸ ውና ከሚናፍቋቸው አምስት ልጆ ቻቸው ተለይተው የካቲት ፳ ቀን



www.ethiopianorthodox.org

፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከጠዋቱ ፲፪ ሰዓት በተወለዱ በ፹፩ ዓመታቸው ከዚህች ዓለም በሞት ተለይተዋል ። አስከሬናቸውም በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከጥዋቱ ፬ ሰዓት ጀምሮ ሙሉ ጸሎተ ፍትሐት ከተደረገለት በኋላ ሥርዓተ ጸሎቱ ሲፈጸም መዘምራኑ የክብር ልብሳቸውን በመልበስ ቀሳውስትና ዲያቆናቱም ጽንሐና መስቀል በመያዝ የሰንበት ት/ቤት አባላትም በግራና በቀኝ ተሠልፈው አስከሬኑ ታጅቦ በመንፈሣዊ ክብር በታላቅ ሥነ ሥርዓት በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን ቤተልሔም ቅጽር ግቢ ውስጥ የካቲት ፳ ቀን ፲፱፹፩ ዓ/ም ከቀኑ በ፲ ሰሰዓት ግብዐተመሬቱ ተፈጽሟል ።

አለቃ ዓለሙ ወንድም ምሉዕ የሆነ ዕውቀት ከመልካም ጠባይ ጋር የነበራቸው ባለአቅማቸውና ችሎታቸው ቤተ ክርስቲያንን ወገንንና ሀገርን ያገለገሉ የቤተ ክርስቲያናችን ደቀመዝሙር ሲሆኑ በተለይም የሀገራችንን የባህል አጻጻፍ ጠንቅቀው ያወቁ ለቤተ ክርስቲያናችን ብዙ የታሪክ መዛግብትን በተለያየ ቦታ በሙያቸው ተጠቅመው ያቆዩና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ ያበረከቱልን የቤተ ክርስቲያን ባለውለታ በመሆናቸው ምንም እንኳ ዛሬ በሕይወተ ሥጋ ቢለዩንም ቤተ ክርስቲያናችን በሕይወተ ነፍስ ስታስታውሳቸው ትኖራለች።


የመካነ ሰማዕት ቅ/ቂርቆስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጽ/ቤት አንዷ ናት ።

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

## ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያንና ልማቷ ፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት እንዳሏት በዓለም ያሉ ሊቃውንትና አገር ጐብኚዎች የመዘክርነት ስፍራ ሰጥተዋቸው እንደሚገኙ ታሪክ ጸሐፊዎች ይመሰክራሉ ፡፡

ከጥንታዊያን ገዳማትና አድባራት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የአረጊት ገዳም ቁስቋም ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አንዷ ናት ።



በኤርትራ ሀ ስብከት ሐረጊት ገዳመ ቁስቋም

የአረጊት ገዳመ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን የምትገኘው በኤርትራ ሀገረ ስብከት በሠራዬ አውራጃ በደገርዋ ከተማ ክልል ሲሆን በዘመነ ብሉይ መሥዋዕተ ኦሪት እንደተሠዋባት ከልደተ ክርስቶስ በኋላም በአብርሃ ወአጽብሃ ዘመነ መንግሥት አቡነ ሰላማ (ከሣቴ ብርሃን) ክርስትናን ለመስበክ ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ወቅት አብርሃ ወአጽብሃ ከአክሱም ተነሥተው የክብር ልብሳቸውን ለብሰው እንደተቀበሏቸውና ቤተ መቅደሱም በዚያን ዘመን ታዋቂነት እንደነበረው ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ የኤርትራ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በተገኙበት በ፳/፹፩ ዓ·ም ከቦታው ተገኝተው መምህር አብርሃም ሠምረአብ የገዳሙ አበ ምኔትን ጠይቀናቸው አስረድተውናል ።

የገዳሙ ሥርዓት መቼ እንደተቋቋመና እንደተጠናከረ አበ ምኔቱ ሲገልጹ ሥርዓቱ የተጠናከረው በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት "አኩቴተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ" በሚል ስያሜ መተዳደሪያ የሚሆን ርስት ተሰጥቶ ለብዙ ዘመናት ገዳሚ ስትጠቀምበት ከቆየች በኋላ በመካከል የጠላት ወረራ ስለአጋጠመ ቤተ ክርስቲያኑ ተቃጥሎ መነኮሳቱ ተበትነው ሲኖሩ እቴጌ ስብለ ወንጌል የአፄ ልብነ ድንግል ባለቤት ከመካከል ኢትዮጵያ ተነስተው በዚህችው ገዳመ ቁስቋም ማርያም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ አረጊት ደብርዋ ሲቀመጡ አባ አዕተ ሌዊ የተባሉትን መነኩሴ በእጨጌነት ሾመው ከታቦተ ማርያም ጋር ታቦተ ሥላሴን ጭምር አስገብተው እንደ ገደሟትና በአካባቢው እግዚእ ሐፀረ ተብሎ የሚጠራ ሰፊ ቅጥር ግቢ ሠርተው ኢትዮጵያ ሀገራችንን ለመርዳት የመጡ ፬፻ የሚሆኑ ፖርቱጋሎችን ይዘው በዚሁ ገዳም አካባቢ ተቀምጠው እንደነበር ገልጸውልናል ።

ከዚያም ወዲህ አፄ ዮሐንስ አራት ግብፃውያን ጳጳሳትን ይዘው በዚህችው ገዳም ሲቀመጡ ቤተ ክርስቲያኑን ለማደስ የአካባቢውን ሕዝብ በማስተባበር ከአካለ ጉዛይ አውራጃ ብዙ ጽዶች ከአሰበሰቡ በኋላ ድርቡሽ የተባለ ጠላት ስለተነሣባቸው የኢትዮጵያ አገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር ሲሉ መተማ በመሔድ ከጠላት ጋር ሲዋጉ ከዚያው ስለአረፉ በዚያ ተከማችቶ የቆየውንና ለቤተ ክርስቲያኑ መሥሪያ ይሆናል የተባለውን ጽድ ፋሽሽት ኢጣሊያ ከምዕዋ ድባርዋ ለመግባትና ለመያዝ አመቺ ጊዜ ስለአገኘ ለገዳሙ የተሰበሰበውን በመዝረፍ ከድርዋ እስከ መንደፈራ ከተማ አስተክሎ ለስልክ መጠቀሚያ እንዳደረገውና በዚህ ምክንያት ታሪካዊነቷ ጠፍቶ ለብዙ ዘመናት እንደቆየ መምህር አብርሃም አስረድተውናል ።

የገዳሙ አበምኔት ይህ ገዳም ከአሁን ከአለበት ደረጃ እንዲደርስ ሲያብራሩ ከ፲፱፻፷፰ ዓ·ም ወዲህ ግን ገዳሙ እየቀናና እየተጠናከረ በመምጣቱ መናንያን መነኮሳትና መነኮሳይያት አርድእትና ተማሪዎች ሠርዓተ ገዳምን በመከተል በማኅበራዊ ኑሮ ፀንተው ገዳሙን በመጠበቅና በማስጠበቅ አካባቢውን በማልማትና በማስገንባት እየሠሩና እያገለገሉ ይኖራሉ ። ቤተ ክርስቲያኑም በዘመናዊ ሕንፃ ተሠርቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ብለዋል ።

ልማትንም በተመለከተ የመነኮሳትና የመነኮሳይያት መኖሪያ ቤቶች ከ፸፭ በላይ የሚሆኑ ክፍሎች ፡ የማኅበረ ምርፋቅ የመንፈሳዊ ትምህርት ለከብትና ለበጐች እርባታ ቤቶች የውሃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች ፡ ሀ/በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ፡

ለ/በመንፈሳዊ ት/ቤት አጠገብ

ሐ/በማኅበረ ምርፋቅ ቅጽረ ግቢ ተሠርተው ግልጋሎት በመስጠት ላይ እንደሚገኙ በዓይናችን ተመልክተናል ።

እንዲሁም መነኮሳቱና መነኮሳይያቱ አርድእትና ተማሪዎች በመተባበር በገዳሙ አበምኔት የጋራ አመራርና አሠራር ፲ ኪሎ ሜትር ያህል ጥርጊያ መንገድ ከዴባርዋ ከተማ እስከ ገዳሙ ድረስ በመቆፈርና በማስተካከል ያለምንም ችግር መኪና እንዲገባ አድርገዋል ።

በተጨማሪም ወይራዎችንና ሌሎች የተለያዩ ዕፀዋትን በመትከል የገዳሙ አካባቢ በዛፎች እንዲዋብ በመደረጉ ለቤተ ክርስቲያኑ ግርማና ድምቀት ሰጥቶታል ።

በአካባቢው ያለ ሕዝበ ክርስቲያንም ሆነ ሌሎች እማንያን ፈውስ የሚያገኙበት ፀበል በጽዳት እንዲጠበቅ በመደረጉ ብዙ ሰዎች እየተጠመቁ የዳኑ መሆናቸውን ከገዳሙ ጽ/ቤት በአለው መዝገብ ተረድተናል ።

በዚህ ገዳም የተሠራውን የሥራ ውጤት ስንመለከት በገዳሙ አበምኔት ሠርቶ በማሳየት የተከናወነ በመሆኑ የሌሎች ገዳማት አበምኔቶች ጊዜ አጋጥሞአቸው ቢመለከቱ በዚህ ዓምድ ከቀረበው ጽሑፍ ይልቅ አይቶ መረዳቱ በቂ ምስክር ስለሚሆን ክርስቲያኖች የሆኑ ሁሉ እንዲጐበኙላቸውና እንዲመለከቱላቸው የገዳሙ አበምኔት መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ።

በበኩላችንም እንዳየነውና እንደተረዳነው ምግብ ለሥራ በተሰኘው ርዳታ ብቻ የላም ና የበግ ርባታ በማቋቋም ፡ እንዲሁም የገዳሙ ይዞታ የነበረውን መሬት አንዳንድ ግለሰቦች ሲጠቀሙበት ከቆዩ በኋላ ለማረስ ባለመቻላቸው የገዳሙ አበምኔት ፳ ጥንድ በሬዎች ገዝተው ራሳቸውም እያረሱ ሌሎችም የዚሁ ተካፋይ እንዲሆኑ ከአደረጉ በኋላ እንደ ይዞታ አድርገው ለቆዩት ገበሬዎች ሲሶ አበል በመስጠትና ሌላውን በገዳሙ የሚኖሩት እንዲጠቀሙበት ሆኖአል ።

ስለዚህ የገዳሙን ሥርዓት ጠብቆና የልማት ሥራዎች እንዲስፋፉ ጥረት ያደረጉት መምህር አብርሃም ሠምረአብ ያሠሩት ሕንፃ ቤተ ክርስቲያንና በአካባቢው የሚገኙት የልማት ሥራዎች ከአምስት መቶ ሺህ ብር በላይ የሚገመት መሆኑን ስለተረዳን ይህን ዓይነቱን የሥራ ውጤት የሚመለከተው ሁሉ በቦታ ተገኝቶ እይዪችሁ በርቱ የሚል የሞራል ድጋፍ ቢሰጥ ከዚህ በበለጠ እንደሚስፋፉ ተስፋ እናደርጋለን።

ሊ·ል ነ ወ





www.ethiopianorthodox.org

# ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስወጳውሎስ (ጴጥሮስና ጳውሎስ)

ቅዱስ ጴጥሮስ ዮና ከሚባል ሰው በቤተ ሳይዳ ተወለደ ቤተ ሳይዳ በገሊላ አውራጃ በባሕር ዳርቻ የምትገኝ አገር ናት ፤ የዮና ትውልድ ከነገደ ሮቤል ነው ዮና ከዘብዴዎስ ጋር ዓሣ እያጠመደ የሚኖር ሰው ነበር ።

ዮና ከነገደ ስምዖን የምትሆን ሴት አግብቶ ቅ/ጴጥሮስን ወለደ ቅ/ጴጥሮስ በተወለደ በስምንተኛው ቀን እንደ ሕገ ኦሪት ተገረዘ ስሙንም በእናቱ ነገድ ስምዖን ብለው ሰየሙት ።

በተወለደ በአምስት ዓመቱም በቤተ ሳይዳ አጠገብ ወደነበረው ወደ ቅፍርናሆም ቤ/መቅደስ ወስደው ሕገ ኦሪት እንዲማር አደረጉ። ቅ/ጴጥሮስም በቅፍርናሆም እንደ አባቱ ዓሣ እያጠመደ ይኖር ነበር በዚሁ ሥራ እንዳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዝሙርነት ጠራው ።

ቅዱስ ጴጥሮስ ፈጣን ፡ ችኩልና ድንጉጥ እንደነበር ሊቃውንት ይናገራሉ ፤ ጌታችን በባሕር ላይ ሲሄድ አይቶ ጌታ እኔም በባሕሩ ላይ እየተራመድሁ ወዳንተ እንድመጣ ፍቀድልኝ ብሎ ለመራመድ ሞከረ ። ነገር ግን ከእምነቱ ሕጸጽ የተነሣ ሊሰጥም ጀመረ በዚሁ ጊዜ ጌታችን ወደ መርከቡ አወጣውና ገሠጸው ።

ጌታችን በቂሣርያ ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ቢጠይቅ ቅ/ጴጥሮስ በፍጥነት ተነሥቶ አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ብሎ መልሶለታልና ምስክርነቱም ትክክል ስለሆነ ጌታችን ብፁዕ ነህ ብሎታል ፤ የመንግሥተ ሰማያትንም በር መክፈቻ ሥልጣን ሰጥቶታል ።

በስድስተኛውም ቀን ሦስቱን ደቀ መዛሙርት ይዞ በገሊላ አውራጃ ከናዝሬት በስተምሥራቅ በኩል ወዳለው ረዥም ተራራ (ደብረ ታቦር) አውጥቶ ጌትነቱንና ክብሩን አሳያቸው በዚሁ ጊዜ ቅ/ጴጥሮስ ጌታሆይ ለአንተና ለኤልያስ ለሙሴም አዳራሽ ሠርተን በዚህ ብንሆን (ብንኖር) ለእኛ መልካም ነበር ብሎ እንደተናገረ በቅ/ወንጌል ተጽፎአል ። (ማቴ. ፲፮ ፡ ፲፯—፩።)

እስራኤላዊ የሆነ ሁሉ በስምንት ዓመቱ ለቤ/መቅደስ የብር እኩሌታ) አንድ አላድ (ግብር ይከፍል ነበር ስለዚህ ቅ/ጴጥሮስም በጌታ ትእዛዝ ከዓሣ ሆድ አራት ድራም አውጥቶ በጌታና በራሱ ስም ገብሮአል ። ቅ/ጴጥሮስ ሁሉን ትቶ ጌታችንን መከተሉንና ዋጋውም ምን እንደሆነ ጌታችንን ጠይቆአል ጌታችን ግን የተደራረበ ሹመትና ክብር ሰጥቶታል። (ማቴ.፲፱—፳)

ጌታችን የደቀመዛሙርቱን እግር ባጠበ ጊዜ ቅ/ጴጥሮስ በፍጹም አታጥበኝም ብሎ እምቢ አለ ጌታችን ግን እኔ ካላጠብሁህ ከእኔ እድል ፈንታ የለህም ብሎ እንዲታጠብ አድርጎታል ጌታችን በተያዘ ጊዜ ቅ/ጴጥሮስ ፈጥኖ ካደ ነገር ግን ፈጥኖ ንስሐ ገባ ቅ/ጴጥሮስ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ ለማየት ታደለ ከትንሣኤ በኋላም በባሕረ ጥብርያዶስ ጌታችንን ለማየት በቅቶአል ። ጌታችን ቅ/ጴጥሮስ ትወደኛለህን? ብሎ ሦስት ጊዜ ከጠየቀው በኋላ በጎቼን ፡ ጠቦቶቼን ጠብቅ ሲል የክርስቲያኖች መሪና ጠባቂ እንዲሆን አደራ ሰጥቶታል ።

ጌታችን ቅ/ጴጥሮስን በምን ዓይነት ሞት እንደሚሞት አስቀድሞ ነግሮታል ቅ/ጴጥሮስ በይሁዳ ምትክ ሌላ ሰው ለመምረጥ ባደረገው ንግግር መንፈስ ቅዱስ ስለተጨመረበት ማትያስ በዕጣ ተመርጦ ከሐዋርያት አንድነት ተቆጥሮአል በቅ/ጴጥሮስ ስብከት በአንድ ጊዜ ሦስት ሺህ ሕዝብ አመነ ቅ/ጴጥሮስ አንድ ኤንያ የሚሉት አንካሳ ፈውሶአል እንዲሁም በሐናንያና በሰጲራ ላይ የሰጠው ፍርድ ለሞት ቅጣት አብቅቶአቸዋል ።

ቅ/ጴጥሮስ በሰማርያ ፡ በኢዮጴና በልዳ እየተዘዋወረ ባስተማረበት ጊዜ ጣቢታ የምትባል ብላቴና ከሞት አስነሥቶአል ቅ/ጴጥሮስ ባየው ራእይ የቆርኔሌዎስን እምነት ተረዳ ፡ ቅ/ጴጥሮስ የወንጌልን ቃል በማስተማሩ ታሥረ ፡ ምእመናን በአንድነት ስለጸለዩለት ግን በጌታ መልአክ ኃይል ከወሕኒ ቤት ወጣ እንዲሁም ከሐዋርያት ጋር ሆኖ በሲኖዶስ ወስኖ ክርስቲያኖችን ከኦሪት ቀምበር ነፃ አወጣቸው ።

ቅ/ጴጥሮስ ለእብራውያን ምእመናን ሁለት መልእክታት ጽፎአል በ፷፯ ዓ.ም ወደ ሮም ገብቶ ወንጌልን በማስተማሩ ተይዞ ከታሠረ በኋላ ኔሮ በስቅላት እንዲቀጣ ፈረደበት ።



## ቅ/ ጳውሎስ

ቅ ጳውሎስ ትውልዱ ከአብርሃም ዘር ከነገደ ብንያም ነው (ፊል ፫.፲፭።) የአያቱና የቅድመ አያቱ አገር ገሊላ ነበር አባትና እናቱ ግን የተመቸ ኑሮን ለመፈለግ ከገሊላ ወደ ኪልቅያ ሄዱ በዚያም ትልቅ ሁከት ስለተነሣ ለቀው ወደ ጠርሴስ ከሄዱ በኋላ ቅ ጳውሎስ በጠርሴስ ተወለደ ።

ጠርሴስ የኪልቅያ የባሕር ጠረፍ ከተማ ነበረች ጠርሴስ ምንም እንኳ ተራራማ ብትሆንም ለምና ፍሬያማ ስለሆነች ፡ ለኑሮ የተመቸች አገር ነበረች በሜዲትራንያን ባሕር ወደ አውሮፓና ወደ ኪልቅያ ለሚተላለፉ ለምሥራቅ ነጋዴዎች አማካይ ነበረች ፡ ብዙ የእጅ ሥራ ይሠራባት ነበር "ይልቁንም በድንኳን ስፌት ሥራ በጣም የታወቀች ነበረች ቅ ጳውሎስም በዚህች ከተማ የድንኳን ስፌት እንደተማረ ተረጋግጦአል በዚህ ምክንያትም ነፃ የወንጌል ትምህርት እየሰጠ በድንኳን ሥራው ይተዳደር ነበር ።

በዚያን ዘመን ጠርሴስ በእስያ ክፍል የምዕራቡና የሰሜኑ አገሮች የሚገዙት ሮማውያን ስለነበሩ ጠርሴስ ዋና የሮማውያን ከተማ ሆና ነበረች ። ስለዚህም ከጠርሴስ ከተማ የሚወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ እንደሮማዊ ይቈጠር ነበር ።

በኪልቂያና በጠርሴስ የሚኖሩ አይሁድ በጣም ጥቂቶች ስለነበሩ በግሪካውያንና በሮማውያን ቋንቋ ይናገሩ ነበር እንጂ በዕብራውያን ቋንቋ አይናገሩም ነበር የቅ ጳውሎስ አባት ግን በሀገሩ ሳለ የእብራይስጥ ቋንቋ አጣርቶ ያውቅ ነበርና ቅ/ጳውሎስ በተወለደ በአምስት ዓመቱ የዕብራይስጥ ቋንቋም ሆነ ሌላውን በኦሪት የታዘዘውን ሁሉ ያጠና እንደነበር ተረጋግጦአል (ዘዳ.፮ ፬ዘኁል፲፭ ፴፯ ፵፩)።

ቅ ጳውሎስ ፲፭ ዓመት በሆነው ጊዜ በአባቱ ፈቃድ ለትምህርት ወደ ኢየሩሳሌም ተላከ በኢየሩሳሌም ባል አግብታ ልጆች ወልዳ የምትኖር ባለትዳር እህት ስለነበረችው ያለችግር ትምህርቱን በገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ ሊማር ችሎአል አይሁድ ጌታችን ባረገ በሰባተኛው ወሩ እስጢፋኖስን በድንጊያ ወግረው ሲገድሉት ቅ ጳውሎስ በምክሩ አባሪ ተነባባሪ ነበር ገድለውት እስኪመለሱም ልብሳቸውን ሲጠብቅላቸው የነበረው ቅ ጳውሎስ ነበር ።

አይሁድ እስጢፋኖስን ከገደሉት በኋላ ስምንቱ ሺህ ማኅበረ እስጢፋኖስ በኢየሩሳሌም ለመኖር የማይቻላቸው ስለሆነ በየሀገሩ ተበትነው በየመንደሩና በየተራራው እየወጡ ወንጌልን በማስተማራቸው ብዙ ሰዎች በክርስቶስ አመኑ ቅ ጳውሎስ ይህን በሰማ ጊዜ ለሕገ ኦሪት ሃይማኖት ቀናኢ በመሆኑ ክርስቲያኖችን ለማስያዝ (ለማሠር) ከኢየሩሳሌም ባለሥልጣኖች ፈቃድ ተቀብሎ ወደ ደማስቆ ሄደ ። በዚያም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሐዋርያነት ተግባር ጠራው ቅ ጳውሎስም በአድራጎቱ ተጸጽቶ ንስሐ ገብቶ የወንጌል አስተማሪ ለመሆን ታጥቆ ተነሣ ።

አይሁድ ደግሞ ቅ ጳውሎስን ለመግደል ይፈልጉት ጀመር እርሱ ግን በወንጌል ትምህርት ብዙ ሥራ ሠራ ከዕለታት ባንድ ቀን ቅ ጳውሎስ ለመንፃት ከቂሣርያ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቶ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ስላገኙት ተረባርበው ይዘው አሠሩትና ወደ ቂሣርያ አወረዱት ። በዚያም ነገሩን በፊሊጦስ ላይ ጨርሶ ወደ ቄሣር ይግባኝ አለ ። በቂሣርያም ሁለት ዓመት ታሥሮ ወደሮም ሄደ በሮምም ቤት ተከራይቶ በቁም እስር ሆኖ ወንጌልን እያስተማረ ሁለት ዓመት ቆየ ወንጀል ስላልነበረበትም በሁለት ዓመቱ ተፈታና በትንሹ እስያ አድርጎ ምእመናንን እያጽናና አብያተ ክርስቲያናትን እየጎበኘ ሎዶቅያ ደረሰ።

ቅ/ጳውሎስ በ50 ዓ.ም. በኤፌሶን ከተማ ጣኦታት የሚያመልኩትን ሰብስቦ ቃለ ወንጌል ስላሰማቸው ፈጥነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ ። ነገር ግን ጥቅሙ የቀረበት ድሜጥሮስ የሚባል የጣዖት ሥራ አንጥረኛ የነበረው ሁከት አስነሣበት ከግብረ አበሮቹ ጋር ሆኖም በኤፌሶን ሰላምና ጸጥታ የሚያደፈርሰው ይህ ጳውሎስ የሚባል ሰው ነው በማለትም ከሰው በዳኛ ፊት አቀረበት ዳኛው ግን አስተዋይ ስለነበረ መርምሮ ኃጢአት የለበትም ብሎ በነፃ አሰናበተው እንድሜጥሮስም አፍረው ዝም አሉ ።

በሚቀጥለው ዘመን የነበረው ገዥ ተሽሮ ሌላ ሲሾም ድሜጥሮስ እለእስክንድሮስ ከሚባል አንድ አይሁዳዊ ጋር በመተባበር የሮማን ከተማ ከክርስቲያኖች ግብረ አበሮቹ ጋር ያቃጠለ ይህ ጳውሎስ የሚባል ሰው ነው ብለው ስለከሰሱት ዳኛው ሊቀጣው ፈለገ ጳውሎስም ደግሞ ወደሮም ይግባኝ ስላለ በነገረ ሰሪዎች የቀረበበትን ክስ በደብዳቤ ጽፎ በወታደር አሳጅቦ ወደ ሮም ላከው ።

ቅ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ሰጥቶ በኤፌሶን ሾመው ወደሮም ለመሄድ



www.ethiopianorthodox.org

በተነሣ ጊዜም በብዙ ኀዘንና በል ቅሶ ተለያዩ "ከቅ/ጳውሎስ ጋር ወደሮም የሄዱት ፡ ቲቶ ቲቂቆስ ፡ ዴማስና ሉቃስ ፡ ፕሮፌምስና አርስጦስ ነበሩ የሮም ጉዞው በቆሮንቶስ አልፈው በአርድያቲክ ባሕር ተሻግረው ብሪንዲሲ ከሚባለው የኢጣልያ ወደብ ደረሱ ከዚያም አጲን በሚባል ትልቅ አውራ ጎዳና አድርገው ሮም ገቡ ።

የኤፌሶን ወታደሮች ጳውሎስን ከታሠረበት የክስ ደብዳቤ ጋር ለኔሮ እንዲራሴ ለቲጊሊትስ አስረከቡ ። ቲጊሊትስ እጅግ ጨካኝና ክፉ ሰው ስለነበር ቅ/ጳውሎስን ከከፋና ከከረፋ ጠባብ ቤት አስገብቶ ቆልፎ አሠረው በዚህ ወቅት ከላይ የተጠቀሰት ደቀ መዛሙርቱ ከሉቃስ በቀር በሙሉ ጥለውት ጠፉ ስለዚህ ነበር ለወዳጁ ለጢሞቴዎስ" በመሥዋዕት እንደ ሚደረግ የኔ ሕይወት ይሠዋልና የምሄድበትም ደርሶአል..." ካለ በኋላ "በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና" በማለት በመከራው ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ጥለውት እንደሸሹ ያስታወቀው (፪ኛ ጢሞ ፬.፮—፲፫) ቅ/ጳውሎስ በሮም ለፍርድ ቀርቦ ወንጀሉ ቀላል ስለሆነ በእስር ቤት ይቆይ ብሎ ኔሮ ከፈረደለት በኋላ ሮም በክርስትና እምነት ከቤ/ተ መንግሥቱ እስከ መኳንንቱ እየተስፋፋ ሲሄድ አይቶ እንደገና ኔሮ ቃሉን ለውጦ ቅዱስ ጳውሎስን አስጠራው ቅ/ጳውሎስ በኔሮ ፊት ሲቀርብ በቀኝ እጁ ከሰንሰለቱ ጋር መስቀል ጨብጦ በልበሙሉነት ሳይፈራ በድፍረት የክርስቶስን ነገረ መስቀል መስከረ" ኔሮን ቲማርም በቁጣ ቃል የሞት ፍርድ ፈርጀብሃለሁ ሲል ጮኸበት ።

ቅ ጳውሎስም ወደሚገደልበት ሲወሰድ የደስታና የፈገግታ ምልክት በፊቱ ተስሎ ይታይ ነበር እንጂ የፍርሃትና የመርበትበት መንፈስ አልነበረበትም አንገቱንም ለባለ ወጉ አመቻችቶ ከሰጠ በኋላ ራሱ ካንገቱ ተለይቶ ለብቻው ወደቀ" ክርስቲያኖቹም ሥጋውን እንሥተው አንገቱን አጋጥመው ቅ/ጴጥሮስንም ከመስቀሉ አላቅቀው በክብር ገንዘው ባቲካን እየተባለ በሚጠራው ሥፍራ ሁለቱንም ሐምሌ ፭ ቀን ፷፰ ዓ.ም. ቀብረዋቸዋል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያን ለነዚህ ሁለት ታላላቅ ሐዋርያት በስማቸው ታቦት ቀርጻ ቤ/ክርስቲያን አንፃ በያመቱ ሐምሌ ፭ ቀን ስታከብራቸውና ስትመሰክርላቸው ትኖራለች ።

ሊ/ትጉሃን ገ/ክርስቶስ ኃ/ማርያም

## የሴቶች ዓምድ

# "ከማራ ሕይወት ምን እንማራለን"

ለሰው ልጅ ከሁሉ አስቀድሞ ጤናማ ሕይውት ያስፈልገዋል ። ጤናማ ሕይወት ከሌለ ወጥቶ ፡ ወርዶ ሠርቶ ፡ ትዳር ይዞ መኖር አይችልም ። ሥጋዊውንም ሆነ መንፈሳዊውን ሥራ አከናውኖ ዋጋ ለማግኘት የሚችለው የተሟላ ሕይወት ሲኖር ነው ። ይህ ከሆነ እናታችን ማራ ጤናማ ሕይወት እንደነበራት ከተግባሯ እንረዳለን ። ይህችም ሴት የብዙዎቹ አባት ትሆናለህ ተብሎ የተነገረለት የአባታችን የአብርሃም ባለቤት ናት እርሷም በዚህ ዓለም በሕይወተ ሥጋ በነበረችበት ጊዜ የፈፀመችውን ልዩ ልዩ ተግባር እና የነበራትንም ሁሉ እምነት ባስታውስ አሁን ላለው ሕብረተ ሰብ መልካም ምሳሌነት ይሰጣል ብዬ እገምታለሁ።

ማራ መካን በመሆኗ አልፎ አልፎ ከማዘን በቀር ሌላ ጉድለት የማይገኝባት ጠባየ መልካም እና ቁምነገረኛ ሴት እንደነበረች መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ። ዘፍ ፲፯ ፡ ፳፫ ይኸውም ባለቤቷን እና ቤቷን ከልብ የምታፈቅር እራሷን ደስተኛ አድርጋ አብርሃምን ለማስደስት ብዙ ጥረት ከማድረግ አትቦዝንም ነበር ። የመጨረሻ እምነቷንም በፈጣሪዋ ላይ አሳርፋ ትኖር ነበር ። እንደተባለውም ልጅ እስከ ወለደችበት ዘመን ድረስ በቤተ ሰብ ሁሉ ከፍቅር በቀር አንዳች ጭቅጭቅ እንዳልነበረና ጊታዬ እያለች ትታዘዘው እና ታከብረው እንደነበረ ፩ኛ የጴጥሮስ መልዕክት ፫ ፡ ፯ መመልከት ያሻል ።

በሌላ በኩል ደግሞ በገላትያ ም.፬.ቁ.፳፩ ፳፯ እንደምናገኘው አጋር በአረብ ምድር ላለችው ለደብረሲና ምሳሌ ስትሆን ማራ ግን ለተነገረላት ተስፋ ብቁ ሆና ስለተገኘች የመጀመሪያይቱ ኢየሩሳሌም ምሳሌ የመሆን ዕድል አገኘች ። በእንዲህ ያለውም ዕድል እራሷን አዘጋጅታ የተገኘችበት ዋናው ዓላማ ባለቤቷ እንግዳ ወዳጅ እንደመሆኑ እርሷም እርሱን ለማስደሰት ብቻ ሳይሆን ሙሉ ፈቃደኛ በመሆን እንግዶችን እየተቀበለች ትረዳና ታገለግል ስለነበር ነው ።

በዚህ አኳኋን ማራ ወደቤቷ እየመጣ ለሚያድረው ለማንኛውም እንግዳ ሁሉ ፊቷን ሳታጠቁር ግንባሯን ሳታኰሳትር ሁሉንም በፈገግታ ለመቀበል ዝግጁ ነበረች ። ይልቁንም ከበርቴዎችንም ሆነ ድሆችን በአንድ ስለምትመለከት በዚያን ጊዜ ለነበሩት ሴቶች ብቻ ሳየይሆን አሁንም ላሉት ጥሩ ምሳሌ ሆናለች ። በዚህ ሁኔታ የምድር ነገሥታትን እና ሀብታሞችን እየተቀበለች በመጋበዟ ባለቤቷን በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ልታደርገው ከመቻሏም በላይ እራሱንም ተወዳጅ ለማድረግ በቅታለች ።

እንዲህ ያለውንም በጐ ሥራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀጠለች ከመሔዷ የተነሳ የሰማዩና የምድር ገዥ የሆኑት ሥላሴ ከቤቷ ሐምሌ ፯ ቀን በእንግድነት አደሩ ። መልካም እራት አቅርባ ከመመገቧም በላይ በሥጋዊ ብቻ ማይሆን በመንፈስም ጭምር ስለተቀበለቻቸው በፊታቸው ከነባለቤቷ ታላቅ ሞገስን አገኘች ። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በባለቤቷ እና በራሷ ሥራ ስለተደሰተ "የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ሁሉ ወደ እናንተ እመጣለሁ። ሚስትህ ማራም ልጅን ታገኛለች" አለው ዘፍ ፲፰ ፡ ፲ በተስፋ ትም ተስፋ ወራሽ የሆነውን ይስሐቅን ወለደች። ከሥራዋም ፍሬ የተነሳ እስካሁን ድረስ ሙሽሮች ጋብቻቸውን በሚፈፅሙበት ዕለት አዛውንቶች በየተራ እየተነሱ ጋብቻችሁ የአብርሃም እና የማራ ይሁን እያሉ ይመርቋቸዋል። ይህም የማራ ሕይወት ብዙ ሊያስተምረን ይችላል ።

ስለዚህ ሴቶች ለመልካም ሥራ ከተዘጋጁ እና ባለቤቶቻቸውንም ስንል በአብረሃም እና በማራ ለማስደሰት ከሞከሩ ምድራዊውን ብቻ ሳይሆን ሰማያዊውንም ሕይወት ጭምር እንደሚያገኙ ከዚህ የበለጠ ምስክር የለም ። ይኸን መካከል የነበረው ጋብቻ በፍቅር የተሳሰረ ስለነበር መልካም ዘር ከማስገኘታቸውም በላይ እስከመጨረሻው ድረስ ሁለቱም ማይነጣጠሉ ተባብረው በመሥራታቸው እርሱ የብዙዎች አባት እርሷም የብዙዎቹ እናት የመባል ስም አግኝተዋል ። ይህንንም የመሰለው ክብር ሊወርስ የሚቻለው ባልና ሚስት በመቻቻል የኖሩ እንደሆነ ነው ።

ማራ ለባለቤቷ ለአብርሃም ታላቅ ረዳት መልካም አገልጋይ ስለነበረች እርሷ ተጠቅማ እርሱንም እንደጠቀመችው ይነገረናል።

ሴቶች የሆናችሁ ሁሉ ምርጫችሁስ የትኛው ይሆናል ? እግዚአብሔር ወደ እናንተ ዘንድ ለማደር በእንግድነት ቢመጣ እንደ ማራ የልባችሁን በር ከፍታችሁ ታስተናግዱታላችሁን ? እግዚአብሔር በአብርሃም እና በማራ ቤት ብቻ ተወስኖ የሚቀር አምላክ አይደለም ። ተዘጋጅታችሁ ከጠበቃችሁት ወደእናንተም እንደሚመጣ አያጠራጥርም ሆኖም መልካም ምግባርን እና ፅኑ እምነትን ይጠይቃል ። ስለዚህ እንደመልካሚቱ እናታችሁ እንደማራ ለባሎቻችሁ እና ለቤተሰቦቻችሁ እንዲሁም ለእግዚአብሔር መልካም አገልጋይ እንድትሆኑ ሕይወታችሁን አዘጋጁ።

ወ መአዛ አስማማው

# በጐ አድራጊዋ ሴት

ወይዘሮ ዓመተ ጽዮን ገብረ የሐንስ ይባላሉ ፡
የ፹ ዘመን ዕድሜ አላቸው ።

ሃይማኖታቸውን አክባሪ ፡ ሀገራቸውን አፍቃሪ ናቸው መዋለ ዘመናቸውን በመንፈሳዊ አገልግሎት ለማሳለፍ በመወሰናቸው ችግር ለደረሰባቸው አብያተ ክርስቲያናት ከምዕመናን ርዳታ እየጠየቁ ይለግሣሉ ።

የሰውን ፊት ሳይፈሩ እና ሳያፍሩ ምንም እንኳ የሰው ፊት እንደእሳት ቢገርፋቸውም ለእግዚአብሔር ብለው በመታገስ ለብዙ አብያተ ክርስቲያናት ንዋየ ቅድሳት አሟልተዋል ። ከነዚህም ለጊዜው በየአብያተ ክርስቲያናቱ ማኅተሞች ተረጋግጦ የደረሰንን እንደሚከተለው አቅርበናል ።

ኮተቤ አካባቢ ለምትገኘው የኢያቄም ቤተ ክርስቲያን ፡

፩ኛ· ብር ፬፻፶ (አራት መቶ ሃምሳ ብር)

፪ኛ· የቅዳሴ መጽሐፍ

፫ኛ· የማኅሌት መገልገያ ፳፬ ጸናጽልና ፳፬ መቋሚያ

፬ኛ· አንድ መሶበ ወርቅ

፭ኛ· ሦስት ኪሎ ዘቢብ

፮ኛ· የአምስት ልሁካል አልባሳት

፯ኛ· ሰባት አክሊላት

፰ኛ· አንድ ኪሎ ዕጣን

፱ኛ· አንድ አነስተኛ የመፆር መስቀል መዳብ

፲ኛ· አምስት የሰሌን ምንጣፎች

፲፩ኛ· አራት ጋሎን ቀለም

፲፪ኛ· ፳፭ ኪሎ እስቴኮ

፲፫ኛ· ፪ ኪሎ ኮላ

፲፬ኛ· ፩፻ ጧፍ





www.ethiopianorthodox.org

፲፫ኛ· ሁለት ብልቃጥ ቅብዓ ቅዱስ

፲፬ኛ· ሁለት ባለመደገፊያ ወንበር

፲፭ኛ· ሦስት አግዳሚ ወንበር

፲፮ኛ· ፭፻፶ የቅድስት ሐና የመልክዐ መጽሐፍ አበርክተዋል ።

እንዲሁም አዲስ አበባ በመሠረት ላይ ለሚገኘው የቅዱስ ያሬድ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ ይረዳ ዘንድ ከ፳፫·፫·፸፬ እስከ ፴·፭·፸፭ ዓ/ም ድረስ በልመና የሰበሰቡትን ብር ፩ሺህ ብር በደረሰኝ ገቢ ለማድረጋቸው የቀረበው ደረሰኝ ያረጋግጣል ።



በጎ አድራጊዋ ወ/ሮ ወለተ ጽዮን

በሌላ በኩል ደግሞ በአዲስ አበባ የካ ደብረ ሣህል ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሥር ለሚተዳደረዋ ዋሻ ደብረ መንክራት ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን መገልገያ ይሆን ዘንድ ።

፩ኛ· የእመቤታችን ስዕል

፪ኛ· አምስት አክሊል ብልጭልጭ

፫ኛ· አንድ ዓይነት መልኩ መጋረጃ አራት

፬ኛ· አንድ ቅዳሴ ግእዝና አማርኛ

፭ኛ· ሁለት ኪሎ ዘቢብ

፮ኛ· አንድ ጽንሐ

፯ኛ· አንድ ኪሎ እጣን

፰ኛ· መቶ ጧፍ

፱ኛ· ሁለት ብልቃጥ ቅብዓ ቅዱስ

፲ኛ· ፲፬ መቋሚያ

፲፩ኛ· ፲፬ ጸናጽል

፲፪ኛ· ፩ ባኮ ሻማ እርዳታ አድርገዋል ።

በሰአሊተ ምህረት ቅ/ማርያም ቤተ ክርስቲያን ማሳደሻና መገልገያ የሚሆን

፩ኛ· ተአምረ ኢየሱስ አንድ

፪ኛ· የግድግዳ ቀለም አራት ጋሎን

፫ኛ· እስቶኮ ፳፭ ኪሎ

፬ኛ· ኮላ ፫ተኩል ኪሎ

፭ኛ· ዘቢብ ፪ ኪሎ

፮ኛ· እጣን አንድ ኪሎ

፯ኛ· እረጅም ጧፍ ሁለት መቶ

፰ኛ· ሻማ አንድ ባኮ

፱ኛ· ቅብዓ ቅዱስ ሁለት ብልቃጥ አሥረክበዋል

በደብረ ልዑል ቅ/ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ኮተቤ

፩ኛ· ተአምረ ኢየሱስ አንድ

፪ኛ· አክሊል አምስት

፫ኛ· ቅብዓ ቅዱስ ሁለት ብልቃጥ

፬ኛ· ጸናጽል አስራ አራት

፭ኛ· መቋሚያ አስራ አራት

፮ኛ· ዘቢብ አንድ ኪሎ

፯ኛ· ዕጣን አንድ ኪሎ

፰ኛ· ጧፍ አንድ መቶ

፱ኛ· ፕላስቲክ የጠላ መጠጫ አሥራ ሁለት አስረክበዋል ።

ለምዕራፈ ቅዱሳን አባኪሮስ ቤተ ክርስቲያን መገልገያ የሚሆን

፩ኛ· መጽሐፈ ቅዳሴ አማርኛና ግዕዝ አንድ

፪ኛ· ቅብዓ ቅዱስ በብልቃጥ ሁለት

፫ኛ· ዘቢብ ሁለት ኪሎ

፬ኛ· እረጅም ጧፍ ሦስት መቶ

፭ኛ· ዕጣን አንድ ኪሎ

፮ኛ· ጸናጽል አሥራ ሁለት

፯ኛ· መቋሚያ አሥራ ሁለት

፰ኛ· ክብሪት አንድ ትልቅ ባኮ

፱ኛ· ሳሙና በቁጥር ሁለት አስረክበዋል ።

በደብረ ዝቋላ ገዳም እንተደእቲ ደሴት ደብረ ከዋክብት ምስካበ ቅዱሳን

፩ኛ· ሰባት አክሊል

፪ኛ· አንድ የዕመቤታችን ስዕል

፫ኛ· መጽሐፈ ቅዳሴ አንድ

፬ኛ· የቄስ ካባ ሳንቃ (ልብስ) አንድ

፭ኛ· ሁለት ኪሎ ዘቢብ

፮ኛ· ዕጣን አንድ ኪሎ

፯ኛ· እረጅሙ ጧፍ አንድ መቶ

፰ኛ· ጥሬ ገንዘብ ብር ፴ (ሥላሳ ብር) አሥረክበዋል ።

እኒህ በጐ አድራጊት ሴት ወይፈትም በዚሁ መንፈሳዊ ተግባር የሚገፋበት መሆኑን ስለገለጹልን ዝግጅት ክፍላችን የኒህን መንፈሳዊት ሴት መንፈሳዊ አርአያነት ሌሎችም እንዲከተሉ ያለንን ምኞት ስንገልጽ እርሳቸውንም የሚረዱዋት ቤተ ክርስቲያን ረድኤት እንደማይለያቸው ተስፋ እና ደርጋለን ።

ተስፋ ጥሩነህ

---

## የናዝሬቱን ...

(ከገጽ ፰ የዞረ)

ቤተ ክርስቲያን ሥራ ያሳየውን መንፈሳዊ ዓላማ በድጋሚ ለማሳየት ልግሥናውን በስፋት የቀጠለ ስለሆነ በአዲስ አበባና በሌሎችም አካባቢ የሚገኙ ምዕመናን ሁሉ የዚህ ቅዱስ ሥራ ተሳታፊዎችና የናዝሬት መድኃኔ ዓለም በረከት ተካፋዎች ለመሆን የልግሥና እጃቸውን እንዲዘረጉልን ይለመናሉ ሲል የኮሚቴው መግለጫ አሳስቧል ።

ማስረሻ ወ/ዮሐንስ
የኮሚቴው ሰብሳቢ



# ዜና ዕረፍት

## የአባ ወንድም መኰንን አጭር የሕይወት ታሪክ

አባ ወንድም መኰንን ከአባታቸው ከመምሬ መኰንን ወ/ማርያም ከእናታቸው ከወ/ሮ አብቸው ገ ሕይወት በ፲፱፻፶፯ ዓ/ም በጐንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ በፋርጣ ወረዳ ልዩ ስሙ ጭረ አቀና በተባለው ቦታ ተወለዱ ። ከዚያም ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚሁ አውራጃ ፡

፩ኛ = አዛውር ኪዳነ ምህረት በተባለው ስፍራ ከመርጌታ ገ ኢየሱስ የዲቁና ትምህርት ተምረው እንደአጠናቀቁ ወደ አዲስአበባ በመምጣት ከአቡነ ቄርሎስ የዲቁና ማዕረግ ተቀብለዋል ፡

፪ኛ = በዚሁ ሙያቸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ ጎፋይ ጊዮርጊስ ከተባለው ሥፈራ በመሄድ ከመሪጌታ ዐቃውዕ ቅኔ ቤት ገብተው የቅኔ ትምህርት ተምረዋል ።

፫ = አባ ወንድም በዚሁ አውራጃ በእስቴ ወረዳ ልዩ ስሙ አጭቃን ኪዳነ ምህረት በተባለችው ስፍራ ከመሪጌታ ንጉሤ የዜማ ትምህርት ተምረዋል ።

፬ = አባ ወንድም መኰንን በዚሁ አውራጃ በፋርጣ ወረዳ ደንጌል ጊዮርጊስ አባ ወርቅነህ ከሚባሉ መምህር ለመዓርገ ክህነት የሚያበቃውን ትምህርት ተከታትለው አጠናቀዋል ።

አባ ወንድም መኰንን እነኝህን ከላይ የጠቀስናቸውን መንፈሣዊ ትምህርቶች በጥራትና በትጋት ከአጠናቀቁ በኋላ በወላጆቻቸው መልካም ፈቃድና በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግ መሠረት ከወ/ሮ አበጀ ጽጌ ጋር ሥርዓተ ጋብቻቸውን በተክሊል ፈጽመዋል ። አባ ወንድም ከጋብቻቸው ሥነ ሥርዓት በኋላ የቅስና ማዕረግን በአቡነ አብርሃም ተቀብለዋል ።

አባ ወንድም መኰንን በዚሁ የቅስና ማዕረግ አንድም ቀን ስለ ችኝ ደከመኝ ሳይሉ በጭር አቀና ጊዮርጊስ ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ



አባ ወንድም መኰንን እኒህ ነበሩ

በዚሁ አውራጃ በወይ በይኝ ማርያም ቤተ ክርስቲያን በመዛወር በሊቀ ጠበብትነትና በአፈ መምህርነት ማዕረግ ተሹመው አገልግለዋል ።

አባ ወንድም መኰንን አለቃ ክፍሌ የተባሉትን የሥጋ ዘመዳቸውን ለመጠየቅ ወደ ሸዋ ሻሸመኔ እንደመጡ በወቅቱ የአዋሣ ከተማ ነዋሪ ከነበሩ ሽማግሌዎች ባላምበራስ ዘርፉ ዳምጤና ሻምበል አበበ በሻህ ሻሸመኔ ድረስ በመሄድ ወደ አዋሣ ከተማ መጥተው የተለመደውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን እንዲቀጥሉላቸው በመማፀን በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም ወደ ሲዳሞ ክ/ሀገር አዋሣ ከተማ እንዲመጡ አድርገዋል ።

በአዋሣ ከተማ ቤተ ክርስቲያን በወቅቱ ያልነበረ በመሆኑ በከተማው ቤተ ክርስቲያን ለማስተከል ከተቋቋመው ኮሚቴ ውስጥ ተመርጠው አባታዊ ምክር እየሰጡ በማበረታታት ለኮሚቴው አባላት ድጋፍ ሲያበረክቱ ከቆዩ በኋላ አሁን የሚገኘውን የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት ከአባታችን ከብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ እንዲፈቀድ ከወረዳው ባለሥልጣኖች ጋር በመሆን ይርጋ ዓለም ከተማ ድረስ በመሄድ በማስፈቀድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ አባት ሲሆኑ በሞት ከተለዩት ጓደኛቸው ከአባ ኃይሌ አወቀ ጋር በመሆን የቅዱስ ገብርኤልን ጽላት ይዘው ወደ አዋሣ በመምጣት መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን አበርክተዋል።

አባ ወንድም መኰንን በመንፈሣዊ አባትነታቸውና በፈጸሟቸው ሕያው በሆነ ሥነ ምግባራቸው የአዋሣ ቅዱስ ገብርኤል ካህናት ፡ ዲያቆናትና ምእምናን በአንድ ድምፅ በመምረጥ በ፲፱፻፷፯ ዓ/ም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲናዊ ተራድኦ መምሪያ የካህናት ማሠልጠኛ ት/ቤት ገብተው ለአንድ ዓመት የተሰጠውን ኮርስ ተከታትለው በትምህርት ቤቱ ይሰጥ የነበረውን ትምህርት ተምረው ተመርቀው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

አባ ወንድም መኰንን የአዋሣ ደብረ ምህረት ቅዱስ ገብርኤልን በቅስና ሙያቸው ብቻ ሣይሆን ከ፲፱፻፷፰ ዓ/ም እስከ ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ድረስ በግብዝና ደከመኝ ሰለቸኝ ሣይሉ መላ የሕይወት ዘመናቸውን ለቤተ ክርስቲያን አገልግ



www.ethiopianorthodox.org

ሎት የሰጡንቱ ፡ ቀልጣፋና ትሑት መንፈሳዊ አባት ነበሩ ። አባ ወንድም መኰንን አዲስ በመሥራት ላይ ለሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በኮሚቴ አባልነት ፡ በአስተባባሪነትና በቀስቃሽነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሲያበረክቱ ቆይተዋል ።

አባ ወንድም መኰንን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን እያበረከቱ ከባለቤታቸው ከወ ሮ አሁን (እማሆይ) አበጀ ደጌ ጋር ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ ም የምንኩስናና ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፱ ዓ ም የቁምስና ማዕረግ ከብፁዕ አባታችን ከአቡነ በርተሎሜዎስ የሲዳሞ ክፍለ ሀገር ሊቀ ጳጳስ ተቀብለዋል ።

አባ ወንድም መኰንን የ፬ ወንዶች ልጆች አባትና ለልጆቻቸው መከታና አለኝታ ነበሩ ፡ አባ ወንድም መኰንን ለብዙ ዓመታት የአዋሣን ደብረ ምህረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሲያገለግሉ ከቆዩ በኋላ አቅማቸው እየደከመ በመሄዱ በሰበካ ጉባዔውና በራሳቸው ፈቃድ ጡረታ ወጥተው በዚሁ ደብር ከአገልግሎቱ ሚይገለሉ ክርስቲያኖችን ሲመክሩና ሲያስተምሩ የተጣላን ሲያስታርቁና የንስሐ ልጆቻቸውን እየጐበኙ በጠቅላላው ሙሉ ግልጋሎት ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ አምላክ የወሰነላቸው ዘመን ስለአለቀ በተወለዱ በ91 ዓመታቸው ታመው በአልጋ ላይ ከዋሉ በኋላ መጋቢት ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

የአባ ወንድም መኰንን አስከሬን በአዋሣ ደብረ ምህረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ጸሎት ከተደረገለት በኋላ መጋቢት ፲፬ ቀን ፲፱፻፹፩ ዓ/ም ቤተሰቦቻቸው ወዳጅ ዘመድና ምእመናን በተገኙበት የቀብራቸው ሥነ ሥርዓት በደብረ ምህረት ቅ/ገብርኤል ቤ/ክርስቲያን ተፈጽሟል ።

የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት

ሊ. ካህናት ኃይለ ሥላሴ

## ጤናችን

በዚህ ዓምድ ከተለያዩ የጤና ባለሙያዎችና ልዩ ልዩ የጤና ነክ ከሆኑ መጻሕፍት ነጥቦች በማዘጋጀት የምናቀርብ መሆናችንን ለአንባብያን እስገንዝበናል ።

ከዚህ ቀደም ሲል "ተላላፊ በሽታና ክትባት" በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ሲዊድን ሕፃናት ሕክምና ክሊኒክ የእናቶችና ሕፃናቶች ጤና ማስተባበሪያ ክፍል ከታተመው መጽሔት ስለኩፍኝ መከላከያውንም በመጨመር እንመለከታለን ።

### የኩፍኝ በሽታና መከላከያው ፡

ኩፍኝ በሽታ በሀገራችን ጐላ ብሎ የሚታወቅ ነው ይህ የኩፍኝ በሽታ በአንዳንድ ክ ሀገር "እንክሊስ" ተብሎ ይጠራል በሽታው በሀገራችን ውስጥ የብዙ ሕፃናትን ሕይወት በማጥፋት የታወቀ በመሆኑ የሚያስፈራ በሽታ ነው።

ይህ የኩፍኝ በሽታ የሚጠነክረውና እየተባባሰ የሚሄደው ጠቅላላ ጤንነታቸው ባልተጠበቀ የምግብ እጥረትና የተቅማጥ በሽታ ባለባቸው ፡ እንዲሁም የእናታቸውን ጡት በማይጠቡ ሕፃናት ላይ ነው ።

የኩፍኝ በሽታ ሕፃናትን እስከ ሞት ሊያደርስ የሚችለው ራሱ ኩፍኝ በሽታ ብቻ ሳይሆን አደገኛ የሆኑ ሌሎች በሽታዎችን አስከትሎ በመምጣት ነው ፡ ይኸውም አደገኛ ከሆኑት ጠንቀኛ በሽታዎች መካከል የሳንባ ኒሞኒያ (በሽታ) ሕመም የልብና የኩላሊት በሽታዎች ናቸው ።

የኩፍኝን በሽታ የሚያመጣው ምንድነው? ከአንዱ ወደሌላው የሚተላለፈውስ በምን ዓይነት ነው? አዎ የኩፍኝን በሽታ የሚያመጣው በዓይን የማይታይ ረቂቅ ሕዋስ ነው ፡ ከአንዱ ወደሌላው የሚተላለፈው ደግሞ ቢባል ፡ በትንፋሽ ሕመሙ ከያዘው ሰው ጋር የቅርብ ግንኙነት በማድረግና ሕመምተኛው በተጠቀመባቸው ዕቃዎችና ልብሶች በመጠቀም ነው ።

እዚህ ላይ በሀገራችን እንደልምድ ሆኖ በብዙዎች ወላጆች እንደሚታመነው የኩፍኝ በሽታ የሚመጣው በሰው ዓይንና (በ·ዳ) በጥላ ይመጣል ወይም ይበረታል ይባላል።

እንደ ሳይንሱ አባባልና እውነታው ይህ ኩፍኝ በሽታ በሰው ዓይንና በጥላ የሚመጣና የሚበረታም አለመሆኑን መገንዘብ አስፈላጊ ነው ጠቃሚም ነው ።

የኩፍኝ መሠረታዊ አመጣጡና አጀማመሩ እንደጉንፋን ሆኖ የጉሮሮ ሕመምና ትውከት ፡ ትኩሳት በአፍንጫ የውሃ መንዘርዘርና የምግብ ፍላጐት መቀነስን ያስከትላል እነዚህ ምልክቶች መታየት በጀመሩ በአራት ቀናት ገደማ ውስጥ ሽፍታው ይመጣል።

ወይም ይታያል ። አመጣጡ ወይም አወጣጡ በመጀመሪያ ግንባርና (ፊት) ላይ ሲሆን ቀጥሎም በሌላው የሰውነት ክፍሎች ላይ ይሰራጫል ።

የኩፍኝ በሽታ ከፈንጣጣ የሚለየው በምንድነው? ስንል ደግሞ የኩፍኝ በሽታ ከፈንጣጣ የሚለው የኩፍኝ በሽፍታ እንደጤፍ ትንሽ ሲሆን የፈንጣጣ ደግሞ ከፍ ያለ ሆኖ መሐከሉ መግል ይቋጥራል ።

እዚህ ላይ ልንገነዘብና ልንረዳው የሚገባ ቁም ነገር አለ ፡ ይኸውም የኩፍኝ በሽታ መታየት የሚጀምረው የበሽታው ሕዋስ ወደ ሰውነት በገባ ወይም ጤነኛ ሰው ሕመሙ ከያዘው ሰው ጋር በተገናኘ በአስር ቀናት ገደማ ነው።

ሌላው ጥንታዊና ባሕላዊ እምነት ሆኖ የቆየ አፈጻጸም እንዳለ የሚታወቅ ነው ይህም ኩፍኝ የያዘው ሕፃን ገላውን በውሃ የታጠበ እንደሆነ ወይም መርፌ የተወጋ እንደሆነ በሽታው ወደ ሆዱ በመግባት ከሞት ያደርስዋል የሚል ሲሆን ከዚህም ጋር ንፍሮ ቀቅሎ ቆሎ ቆልቶ ፡ ቂጣ ጋግሮ ሎሚ ገዝቶ ወደ ውጭ በመርጨት የኩፍኝ በሽታ ሕመሙ ቀላል እንዲሆን ያስችላል የሚለው አባባል ከእውነት የራቀ መሆኑን ማይንሱ ያስገነዝባል ።

በመንፈሳዊውም በኩል እምነትን በአንድ አምላክ ላይ መጣል እንጂ እህልን በመሬት መርጨት ከእምነት ውጭ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያን ይህን አይነቱን አፈጻጸም ትቃወማለች ።

በለጠ አበበ

# ሐዋርያው ናትናኤል

ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል የተወለደው በናዝሬት ውስጥ በቃና ዘገሊላ ነው ። የአባቱ ስም ቀለዮጳ ይባላል የመጀመሪያው ስሙ ስምዖን ነው የቅጽል ስሙ ናትናኤል ነው ናትናኤልም ማለት ስጦታ ሀብተ እግዚአብሔር ማለት ነው ። ትውልዱም ከነገደ ብንያም ነው ይህንም ሐዋርያ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዋርያት ፲፪ኛ አድርጐ መረጠው በተራ ቁጥርም ፲፪ኛውን ክፍል ይዞ ይገኛል ።

ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል በኢየሩሳሌም ከሐዋርያው ከቅዱስ ያዕቆብ ቀጥሎ ምሁረ ኦሪት ስለሆነ ኤጲስ ቆጶስነት ተሹሟል። ለሐዋርያነትም ከመመረጡ በፊት ለሕገ ኦሪት ቀናተኛ ፈሪሳዊ ነበር ይኸውም ለሕገ እግዚአብሔር ነው ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራሁለቱን ሐዋርያት ሰባ ሁለቱን አርድእት ሰላሳ ስድስቱን ቅ· አንስት መርጦ ፫ ዓመት ከ፫ወራት ከአስተማራቸው በኋላ እንግዲህ ወደ ዓለሙ ሂዱ አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ አላቸው ማቴዎስ ፳፰ ቁጥር ፲፱

ሐዋርያትም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ በመቀበል ለአንድ ዓመት ያህል አብረው በኢየሩሳሌም በአንድነት ከኖሩ በኋላ ይኸንን ዓለም ለማስተማር በዕጣ ተከፍለው ለስብከተ ወንጌል ተሰማርተዋል ። ዕጣም በተጣጣለ ጊዜ ለቅዱስ ናትናኤል ምድረ ግብፅና በስተሰሜን የሚገኘው አፍሪካ ደረሰው ሐዋርያው ናትናኤል ወደ ሀገረ ስብከቱ ግብፅ ገብቶ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ለማስተማር ከመጣ ጀምሮ ለሰው ልጅ ሁሉ የሰራውን ተዐምራት ትክክለኛና ለሕይወት ጠቃሚ መሆኑን በመግለጽ ብዙ አረማውያንን አሳምኖ አጥምቆአል ከዚህ በኋላ ከገቢረ ኃጢያት ወደ ገቢረ ጽድቅ ከአምልኮተ ጣኦት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ከመጥፎ ተግባራቸውና ሥራቸው ብዙ አረማውያንና አህዛብ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ አድርጓል ። ከዕለታት አንድ ቀን ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ወደ ገሊላ ሲመጣ ሐዋርያው ፊልጶስን በመንገድ አገኘውና ና ተከተለኝ አለው ፊልጶስም ናትናኤልን ጠርቶ እንዲህ አለው ሙሴ በኦሪት ነቢያት በትንቢት የተናገሩለት ኢየሱስን አገኘሁት አለው ። ናትናኤልም በውኑ ከናዝሬት ደግ ነገር ሊገኝ ይቻላልን አለው ፊልጶስም መጥተህ እይ አለውና እየመራ ወደ ኢየሱስ ሲወስደው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ ብሎ ተናገረው ተንኮል ክዳት የሌለበት እውነተኛ የእስራኤል ሰው ነው ባለው ጊዜ ናትናኤልም ወዴት ታውቀኛለህ አለው ። ጌታችንም ፊልጶስ ሳይጠራህ ከበለስ ዛፍ በታች አየሁህ አለው ይህም ማለቱ ሄሮድስ በቤተልሔም ፲፬ ዕልፍ ከ፬ ሺህ ሕፃናትን በአስገደለ ጊዜ እናቱ በቀፎ አድርጋ ከበለስ ሥር ደብቃው ስለነበር ነው ።

ጌታችንም ያን ጊዜ እንዳትሞት ያዳንኩህ እኔ ነኝ ሲለው ነው





www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል ጌታ ደግነቱን ስለመሰከረለት ደስ ብሎት ወንጌልን በሰፊው ለማስተማር ወደ ሀገረ ስብከቱ ምድረ ግብፅና አፍሪካ ገብቶ በየከተማውና በየሀገሩ እየዞረና እየተመላለሰ የእግዚአብሔር ቸርነትን አስተማረ ።

የእግዚአብሔርን አዳኝነት ለአመነበት ሁሉ ከደዌ ነፍስ ከደዌ ሥጋ የሚያድን መሆኑን በማስተማሩ ሕዝቡም ትምህርቱን ተቀብለው ብዙ አረማውያን በወንጌል በማመን ተጠመቁ የክርስቶስ ቤተሰብም ሆኑ ።

ሐዋርያው ናትናኤል አስቀድሞ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ ስለአደረበት ልዩ ልዩ ተአምራቶችን ይሠራ ነበር ፡ ለምጻሞችን አንፅቶዋል ፡ የዕውራንን ዓይን አብርቶዋል ዲዳዎችንም አናግሮአል ፡ ሐዋርያው የሚሰብከው ከዕለታዊ ኑሮ ከሰው ይዞታ ጋር የተያያዘ ስለነበር ሕዝቡ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ እያመነ በመሄዱ አንዳንድ አረማውያን በክርስቶስ ስም ያላመኑ ስለነበሩ በቅናትና በሰይጣን እየተመሩ በጠላትነት ተነሱበት ሁከትን አስነሥተው ከነበረው አምልኮታችን ከሀገራችን መጥቶ ይማንፈልገው ትምህርት ግድ ተቀበሉ እያለ ከሀገራችን ባህልና ልማድ ለሕዝቡ የሐሰት ትምሕርት እያስተማረ አሰምኖ ወሰደው ብለው በዘመኑ ለነበረው ለግብፁ ንጉሥ ለእንድርያኖስ ነገሩት ንጉሡም ይህን በሰማ ጊዜ በኃይል ተቆጥቶ ጭፍሮቹን እንዲያመጡት አዘዘ ፡ ጭፍሮቹም ከሚያስተምርበት ይዘው እያዳፉ ወደ ንጉሡ አቀረቡት ንጉሡም አንተ ይህን እንድታስተምር ማን ፈቀደልህ አለው።

# የናዛሬቱን ...

(ከገጽ ፳፭ የዞረ)

ሲሆን የዚህን ነዳይ ምሳሌነት የተመለከተች አንዲት ግለሰብ

ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤልም ያለ አንዳች ፍርሃት በፈጣሪዬ በእግዚአብሔር ተእዛዝ ነው ባለው ጊዜ ንጉሡ ተቆጥቶ እንዲህ ያለውን እንዳታስተምር አለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል አሰበ ሥጋችሁን ከሚገድሉ አትፍሩ ነፍሳችሁን መግደል አይችሉም እና "ማቴ· ፲· ፳፰

በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ የሥጋውን ሞት ሣይፈራ የእግዚአብሔርን ሕግ እየሰበከ ከማስተማር ማንም ሊከለክለኝ አይችልም ። ባለጊዜ ደፍሮ እንዴት እኔን ንጉሡን ይናገራል ብሎ በጭካኔ ሐምሌ ፲ ቀን በሰይፍ አስገድሉታል ። ስንከማር እንመልከት ሐዋርያው ቅዱስ ናትናኤል ክደትና ተንኮል የሌለበት እውነተኛ እስራኤላዊ ነህ ተብሎአል አሁንም ክርስቲያን በሙሉ ይህንን የመሰለ ምስጋና ሊቀበል ይገባዋል ምክንያቱም በጊዜአችን ተንኰልና ክደት በበዛበት ዓለም ሥጋዊ ጥቅምን በማሳደድ ግብታዊ ሕልፈት ሲመጣ ማረኝ ማረኝ ማለቱ በቂ ልመና ስለማይሆን ንጹሕ ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርስ እምነት ይዘን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ለመገኘት የበቃን በግርምት ዓውድ ከተንኰል የራቃችሁ ወደ እኔ እንዲለን ፈቃዱ ይሁንልን አሜን።

መምህር ወልደ አማኑኤል
ወንድማገኘሁ

ደግሞ ነዳያኑ ለበጐ ሥራ ሲሽቀዳደሙ እየተመለከትኩ እኔ በፈራሽ ሥጋ ላይ ወርቅ አንጠልጥዬ መሄድ አይገባኝም በማለት የጣቷን ቀለበት አውልቃ ተሽጦ ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ እንዲውል ይደረግልኝ ስትል በእርዳታ አበርክታለች ።

የናዝሬቱ መድኃኔ ዓለም ተአምር ሰፊ እንደመሆኑ መጠን ወደፊት በተከታታይ የሚገለጽ ሲሆን አሁን ቤተ ክርስቲያኑ ሊሠራበት የተፈቀደው ሥፍራ ከናዝሬት ከተማ በስተሰሜን በኩል የሚገኝና ትርምስ ከሚበዛበት ከተማ ለየት ብሎ ለምእመናን በፀጥታ የሕሊና ጸሎት ለማድረስ ልቦናን በተመስጦ ወደ ፈጣሪ የሚሰበስብ አካባቢ ከመሆኑ ጋር ከ30.000 ሜትር ካሬ በላይ የሆነ ቦታ በይዞታው ሥር የሚገኝ ስለሆነ የቤተ ክህነቱ እርዳታና ድጋፍ ከተጨመረበት ከቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ጋር በተያያዘ መልኩ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትና ሌሎችም መንፈሳውያን ት/ቤቶችን በጐ አድራጐትን የመሳሰሉ ድርጅቶች ሁሉ ሊሠሩ እንደሚችሉና በእቅድም ውስጥ እንዳሉ ተገልጿል ።

የናዝሬቱ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ይህን በመሰለ ይዞታ የተደራጀ ከመሆኑ ጋር 3. ከፍተኛ በ20. ቀበሌ የታቀፈው የናዝሬት ከተማ ሕዝብ የቀብሩ ሥነ ሥርዓት የሚፈጸምበት መካነ እረፍት ቦታ ስለሆነ ለሥራው አስፈላጊ የሆነው አሥሪ ኮሚቴ ከተዋቀረ አንስቶ ምዕመናኑ ከልብ በመደሰት መንፈሳዊ ስሜቱ ተቀስቅሶ ከአሁን በፊት በቅድስት ማርያም

(ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል)



# ይቅር በላቸው ባይን

| | |
|---|---|
| እንኳን አደረሳችሁ በመላው<br>ለብርሃን ትንሣኤው ። | "ድርሰት" |
| እኔም ለስቅለት ተነሣሁ<br>ለትንሣኤ ደረሥሁ ። | |
| ክርስቲያን ሁሉ ገሥግሥ<br>እስከመስቀል ድረስ ። | (መስቀለ ሞትህን ተሸክመህ ተከተለኝ) |
| ከበረት ወጥቶ ዕሮብ ለታ<br>ወዲያው ደረሰ ላሙስ ማታ ። | (ላም) |
| ተሸጥህ ልምጣ ዐርብ ለት | (በገንዘብ ተሸጠኻል) |
| በግንዳለህ ሙከት | (በግንድ ላይ) |
| ያለበግ ጠቦት አያድርም<br>ያለሙክት ሀብታም | (የዓለሙ እክት) |
| ሀብታምማ የታለው<br>ጠቦት ያለው ደህው ነው | (መጥበብ /ጠቦት) |
| በዚያው ሆነ ወልድ በዚያም<br>በግንዳሠሩት አልቀረም ። | (በግ እንዳሠሩት) |
| ጨካኞች ናቸው ካህናት<br>ወደኋላማ ታሠሩት ። | (የፊጥኝ የኋላውን ሥቃይ) |
| እኔስ አልልህ ወልድ ታሠር<br>ፊቅደህ ከመጣህ ተጠፈር ። | (ከሰማይ ከጠፈር) |
| የለንጊኖስ ጦር እያደረ<br>በቀይ መስቀል ተከበረ ። | (የመስቀሉ ክብር በደሙ) |
| ወጉት ወይ ለካ ጎኑን<br>ይቅር በላቸው ባይን ። | (ዓይን) |
| አሁን ጌታውን ሲሉት ከዳ<br>ምነዋ ስሞት ይሁዳ ። | |
| ምንም ነወር ብል ሰው አክብሬ<br>ቀርበ እግዚአብሔር ዛሬ | (መሞት) |
| አምላክ አዳምን አከበረው<br>ፊጥኖ ተነሥቶ ነወር አለው ። | (ለመስቀል እግዚአብሔር ቀረበ) |
| በፈጠረው ሰው መዳፍ ክንድ<br>ተገረፈ በዓውድ ። | (ትንሣኤውን) |
| ጅራፍ ይዞ ሲገርፍ<br>አያፍርሞይ ያመዳፍ ።፡ | (ያ አመድ አፍ) |
| ከኢየሩሳሌም መቅደስ<br>የወሰደውን ቀሚስ<br>በሮማይስጥ ጲላጦስ ። | (ሮማይስጥ ቋንቋ) |

# የናዝሬቱን ...

(ከገጽ ፳፱ የዞረ)

ግጥን ገቢ ከማድረጋቸውም በላይ ሌሎች አምስት በጐ አድራጊዎች ደግሞ እስከ ዛሬ ድረስ ልቦናቸውን ሲያሳዝነው የቆየው የቤተ ክርስቲያኑ አለመሠራት እንደነበረና ጊዜው ደርሶ ሥራው በመጀመሩ እጥፍ ድርብ ደስታ የተሰማቸው መሆኑን ገልጸው ወደፊትም ሥራው እስከ ተፈጸመ ድረስ በማናቸውም አቅጣጫ እርዳታቸውን እንደማያቋርጡ በማረጋገጥ እያንዳንዳቸው 5,000 (አምስት ሺህ ብር) ለመክፈል ቃል ገብተዋል ።

ከዚህም ሌላ ከአዲስ አባባ መጥተው መጋቢት 27/81 ዓ/ም የመድኃኔ ዓለም በዓል ከተገኙት ምዕመናን መካከል አብዛኞዎቹ ወደፊት የሚሰጡትን እርዳታ በተስፋ ሰነድ ሲያስመዘግቡ ሌሎች ሁለት ግለሰቦች ደግሞ ይህ አሰደሳች መንፈሳዊ ሥራ ሲከናወን በማየታቸው ልቦናቸው መደሰቱን ገልጸው ወደፊትም እርዳታውን እንደሚቀጥሉ በማረጋገጥ እያንዳንዳቸው 1,000 (አንድ ሺህ ብር) ለግለሰዋል ይልቁንም በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ግቢ ወድቆ ከምዕመናን በሚሰጠው ምፅዋት እየተረዳ የሚኖር አንድ ነዳይ በቅጽሩ ወድቁ ከሕዝብ እየተጣለልኝ ያጠራቀምኳት የሳንቲም ድቃቂ ገንዘብ ተከማችታ 100 (አንድ መቶ ብር) የሰጠ

(ወደ ገጽ ፰ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

ቢለዋ ሳለ ጥቁር አፋ (ቀይ አፋ ጐራዳ)
በጉ ተሠዋ በቀያፋ ።
አመጣ ጴጥሮስ ሚዛኑን (ሰይፋን ሊመዝ)
ሊመዝን ይኸን ሰይፋን ።

ጴጥሮስ ቢላውን በመዘዘ (ጨረቃ ደም መምሰሉን)
ጨረቃ በደም ተያዘ ።
ይህንን ነጥብ አስተውሉ (አትቆጡ)
እንዲያው ሳታዩ ቢላ ትበሉ ።
ጴጥሮስ ቢፎክር ምን ቢያጉራራ (ጆሮ መቆረጡን) ጉራ ወረሞ)
በጆሮ አለፈ በጉራ ።
ገሥግሦ እንደጅብ እንደ አውሬ
ይሁዳ ሌሊት መጣ ዛሬ (ከጂ ባይኖር)
ከጅብ ከአውሬ ለምን ይደር
ይሁዳ ከጂብ አይኖር ።
ዘመድማ ዘመድ ነው (ከጅብ አዳነው)
ፈጥኖ ከጂ ባዳናው ።
ድኖ የለሞይ ይዞ ሰይፍ (በአፍ ከጂ)
ያ ስምዖን ጴጥሮስ ከጂባፍ ።
ሸሸ ሕፃኑ ማርቆስ (ቆሞስ አለ)
ቆሞ ሳለ ዮሐንስ ።
ጴጥሮስ ቆጥ አለው? ወይስ ወሬ ቆጥ (ቆጣ አለ)
ምነው ቆጣለ ዛሬ ።
ሐዋርያትም አሚችሁ (በይሁዳ)
ሥጋውን ደሙን በላችሁ
ታዲያ በይሁዳናችሁ ።
ማርያም ከቶ ጠፍቷል ያልሽ (አሑድ በይሁዳ መኖር)
ዐርብ ቅዳሜን ቢለይሽ
እስኪ በይሑድ አለልሽ ።
አትሠጋም አንተ ለሕዝብህ (ሥጋ ወደሙ)
ኧረ ሥጋ አምላክ እባክህ ።
የዓሣ ሥጋ ለመጥበስ
ዘልዝሎ ሰቅሏል ክርስቶስ ።
የበሬ ሥጋ ቢቀርሳ (ነጣ መነስ)
ተሰቀለ ወልድ ነጣ ።
የገሊላ ቤት ታድሷል (ፈርሱ አለ)
የይሁዳ ቤት ፈርሷል ።
ይሁዳ ወድቋል በጉዳት (ያንጀቱ መውጣት)
እየሬቀው አንጀት ።
መ/ዜና ይቁም ይግዛው (ይቀጥላል)

1833
1757
74



# የናዝሬቱን መድኃኔ ዓለም ቤተክርስቲያን ለመሥራት ከሚቴ መቋቋሙ ገለጸ

## በበዓሉ ዕለት ከብር 25,000 በላይ ተገኘ

በምሥራቅ ሸዋ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚገኘው የናዝሬት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን ለብዙ ጊዜ የኖረ በመቃኛ ስለነበረ ይህንኑ ሁኔታ በመመልከት የከተማው ነዋሪ ሕዝብ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ እንዲጀመር ያሳሰፈው ውሣኔ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ቀርቦ ከታየ በኋላ ከሕዝቡ በቀረበው ውሳኔ መሠረት ሥራው እንዲቀጥል መጋቢት 12 ቀን 1981 ዓ/ም ስላተፈቀደ በአንድ ማዕከልና በ6. ንዑሳን የተጠናከረ የአሠሪ ከሚቴ መዋቀሩ ተገለጸ ።

ይህ በመቃኞ የቆየው ቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ በቀረበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት እንዲሠራ ከቅዱስነታቸው መፈቀዱ እንደተሰማ የቤተ ክርስቲያኑ ሁኔታ በዚህ አይነት መቆየቱ ልቦናቸው እያዘነ የሥራውን መጀመር በጉጉት ይጠባበቁ ከነበሩ ምእመናን መካከል ስማቸው ለውዳሴ ከንቱ እንዳይገለጽባቸው የፈለጉ ሶስት ግለሰቦች እያንዳንዳቸው 10,000 (አሥር ሺህ ብር) ወዲያውኑ በታቦቱ ስም በተከፈተው የባንክ

(ወደ ገጽ ፳፭ ዞሯል)

# ልደታ ለማርያም (የማርያም መወለድ)

እመቤታችን ድንግል ማርያም ዓለም ገና ሳይፈጠር በአምላክ ልቡና ታስባ ትኖር እንደነበር በመቅድመ ተአምሯ ተመዝግቧል ይኸው መቅድም አዳምና ሔዋን እምቤታችን ከእነርሱ ልትወለድ ተፈጠሩ ፤ አዳምም ድንግል ማርያም ከእርሱ አብራክ እንድትከፈል ከሔዋን ማኅፀንም እንደምትወለድ አውቆ ሔዋንን ሕይወት ነሽ ይላት ነበር ይላል ።

ከአዳም ጀምሮ እስከ አብርሃም እስከ ሙሴ እስከ ዳዊት ከዳዊትም እስከ ወላጆቿ ድረስ በብዙ ምሳሌ ሲነገርላት የመጣ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ።

ነቢዩ ኢሳይያስ "ትወጽእ በትር እምሥርወ እሴይ ወየዓርግ ጽጌ እምጉንዱ" ከእሴይ ሥር በትር ትወጣለች ከግንዱም አበባ ይወጣል ብሏል ይህንንም ቃል ኢትዮጵያዊው ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በመዝሙሩ ሲገልጽ "ይእቲ በትር አምሳለ ማርያም ቅድስት ይእቲ ወጽጌ ዘወጽአ እምኔሃ አምሳለ ለወልድ "ወደ አማርኛ ሲተረጉም ይህች በትር የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት ከእርሷ የወጣው አበባም የወልድ ምሳሌ ነው ብሏል ትን.ኢሳ.፲፩.፩

እንዲሁም ነቢዩ ሕዝቅኤል "ወደምሥራቅ ወደ ሚመለከተው በስተውጭ ወደአለው ወደ መቅደሱ በር አወጣኝ ተዘግቶም ነበር እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል "በማለት እመቤታችን ድንግል ማርያምን በተዘጋች ቤት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጐልማሳ መስሎ ተናግሯል ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት መውጣቱም በፍጹም ድንግልና ተፀንሶ መወለዱን ያጠይቃል ትን ሕዝቅኤል ፵፬.፩፡፪

ለማስረጃ ያህል መጥቀሳችን ነው እንጂ የተነገሩትን ትንቢቶችና የተመሰሉትን ምሳሌዎች ሁሉ አጠቃሎ ለመናገር አይደለም ፤ እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ ከመወለዷ በፊት የተነገሩ ናቸው እስኪ ደግሞ ወደልደቷ መለስ ብለን ታሪክ እንመልከት ።

የእመቤታችን ድንግል ማርያም ወላጆች ኢያቄምና ሐና ናቸው አባቷ ኢያቄም ከነገደ ይሁዳ ሲሆን እናቷ ሐና ደግሞ ከነገደ አሮን ናት ።

ሁለቱም ደጋግና የእግዚአብሔርን ሕግ ጠባቂዎች ነበሩ የተራበ ማብላት የተጠማ ማጠጣት የታረዘ ማልበስ የተለመደ ተግባራቸው ነበር ። ነገር ግን ልጅ አልነበራቸውም ነበርና ልጅ እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን አዘውትረው ይለምኑት ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ሐና የምልብሰው ልብስ የለኝም እንጂ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄጄ ሰግጄ ጸሎት አድርሼ እመጣ ነበር አለች በሴተኛ አዳሪ የምትኖር አንዲት ጎረቤት ነበረቻትና ልብ ስማ ከእኔ አለልሽ አይደለምን የፈለግሽውን ልብስ ለብሰሽ አትሄጂምን አለቻት ሐናም መልሳ ንጹሐ ባሕርይ እግዚአብሔር ንጹሕ ነገርን ይፈልጋል የአንቺ ልብስ የተገኘው በአሰበ ደነስ ስለሆነ እርሱን ለብሼ ሄጄ አምላኬን ብለምነው ጸሎቴን አይቀበለኝም አለቻት ጐረቤቷም በአነጋገሯ ተናዳ እኔ እስከ ዛሬ ድረስ እግዚአብሔር ለሐና ልጅ የነሣት ለምንድን ነው? እያልኩ አዝንልሽ ነበር ለካስ በዚህ ክፋትሽ ነው ልጅ የነሳሽ ብላ ዘበተችባት ።

ሐና ግን አልቀረችም ያንያላትን ልብስ ለብሳ ከባሏ ከኢያቄም ጋር ሄደዋል ጸሎታቸውን አድርሰው ወደቤታቸው ሲመለሱም በመንገድ ደከማቸውና ከዛፍ ሥር አርፈው ሳሉ አርጋብ ከጫጩቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ ተመልክተው እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! እነዚህን አርጋብ እንዲባዙ የምታደርግ አንተ ነህ እኛን ባሮችህን ከእነዚህ ርግቦች እንዴት አሳነስከን ብለው ምርር ብለው [illegible] ወዲያው እንቅልፍ ይመጣባቸውና ይተኛሉ በራዕይ ሐና የኢያቄም በትር አለምልማ ፤ አብባ አፍርታ ዓለሙ ሲመገባት ታያለች ኢያቄምም ነጭ ርግብ ሰባቱ ሰማያትን ሰንጥቃ መጥታ በሐና ማኅፀን ስታድር ያያል ከእንቅልፋ



www.ethiopianorthodox.org

ቸው ነቅተው ሁለቱም ስለአዩት ሕልም እርስ በእርሳቸው ተነጋገረዋል ።

ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ወዲያው እመቤታችን ድንግል ማርያም በሐና ማኅፀን ትፀነሳለች ለሐና አንድ ዓይዷ የታወረ አክስት ነበረቻት ሐና እግዚአብሔር በረድኤት ጐበኘሽ ብላ ሰውነቷን ዳሳ የታወረውን ዓይኗን ብትነካው በርቶላታል እንዲሁም የሐና የአጐቷ ልጅ ሞቶ ሐና በጣም ትወደው ነበርና የአስከሬኑን የአልጋ ሸንከር ይዛ ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት አፈፍ ብሎ ተነሥቶ ሰላም ለኪ እ እምሔውቱ ለዘገብረ ሰማየ ወምድረ "ሰማይና ምድርን ለፈጠረ አያቱ ሆይ! ሰላምታ ይገባሻል ብሎ ተናግሮ ተመልሶ አርፏል ።

በዚያ ቦታ ተገኝተው ይህንን አስደናቂ ተአምር የተመለከቱ አይሁድ ሳይወለድ ገና በማኅፀን ሳለ ይህንን ተአምር ያደረገ በተወለደማ ጊዜ ምን ያህል ተአምር ያደርግ ይሆን ብለው በእሳት አቃጥለን በደንጊያ ወግረን እንግደላት ብለው በሐና ላይ በጠላትነት ተነሡባት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በራዕይ ተገልጾ ለሐና ወደ አድባረ ሊባኖስ ሂጂ አላት ወደ ዚያ ሄዳ ሊባኖስ በሚባል ተራራ ወልዳታለች ቀደም ሲል ነቢዩ ከሊባኖስ መርዓት ትወጣለች ብሎ የተናገረውም ትንቢት በዚያን ጊዜ ተፈጽሟል ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም ግንቦት አንድ ቀን በተወለደች ጊዜ በዚያው አካባቢ ለስምንት ቀናት ያህል ብርሃን ሆኖ እንደሰነበተ ተነግሯል የሐና ዘመዶችም ዳቦ እየጋገሩ ፡ ቆሎ እየቆሉ ንፍሮ እያነፈሩ ገንፎ እያገነፉ ይዘው ወደሐና በመምጣት ደስታቸውን ገልጸዋል ዛሬም በሀገራችን የግንቦት መባቻ ዕለት ንፍሮ እየተነፈረ ዳቦ እየተጋገረ ፡ ጠላ እየተጠመቀ በአንድ በላይ እየተሰበሰቡ የሚበላ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው መሠረት ነው ።

ነገር ግን በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ መሥመሩን እየለቀቀ ወደአምልኮ ባዕድ ሲያዘግም ይታያል በግንቦት ወር ከመባቻ እስከ አመሰላሳ ባሉት ቀናት ንፍሮ አንፍረን ቆሎ ቆልተን ቂጣ ጋግረን ተሰብሰበን በልተን የተረፈውን በመንገድ ላይ ካልበተን ክረምቱን በጤና ለመክረም አንችልም ጉንፋን ይይዘናል በሽታም ይጸናብናል ይላሉ ።

ሌሎች ደግሞ ከዚህ አልፈው በግንቦት ወር ቦሃ በግ ቀይ ዶሮ ዳንግሌ በግ ገብስማ ሠራን ዶሮ ገዝተን ደም ካላፈሰስን ዑቃቢያችን ተጣልቶ ከበሽታ ላይ ይጥለናል ይላሉ በሌላ በኩል ደግሞ በወርኃ ግንቦት ጋብቻን የሚፈጽሙ ሰዎች ትዳራቸው ሊጸና አይችልም ኑሮቸውም አይቀናም እያሉ ጋብቻን የሚከለክሉ ይገኛሉ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው እምነተ ጉድሎነትን ነው ።

ከላይ እንደተጠቀሰው ግንቦት ልደታ የሚከበረው የዓለም መድኃኒት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘችልን ድንግል ማርያም የተወለደችበት በመሆኑ ነው ይህንን ወደጐን ትቶ ወሩን በሙላ የልዩ ልዩ አምልኮ ባዕድ መፈጸሚያ ማድረግ ተገቢ አይደለም ።

ቤተ ክርስቲያናችን ግንቦት አንድ ቀን (መሠረተ ሕይወት) የሕይወት መሠረት ድንግል ማርያም የተወለደችበት በመሆኑ በስሟ በታነፁ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ በማኅሌት በቅዳሴ አክብራ ትውላለች በአንድ ዓመት ውስጥ ከሚከበሩት የእመቤታችን ዓበይት በዓላትም አንዱና ከፍተኛው ግንቦት አንድ ቀን መሆኑ በነገረ ማርያም ተጽፏል ስለዚህ ይህንን ዕለት ልዩ ልዩ አምልኮ ባዕድ በመፈጸም ሳይሆን በእመቤታችን ስም ወደ ታነፁት አብያተ ክርስቲያናት ሂደን በመጸለይ የተራቡትን በማብላት የተጠሙትን በማጠጣት የታረዙትን በማልበስ ልናከብረው ይገባናል በእኔ አምኖ በአንች በመማፀን የተራበ ያበላውን የተጠማ ያጠጣውን እምርልሻለሁ ብሎ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ኪዳን ሰጥቷታልና ።





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ። ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋሪያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ·
የመልእክት ሣ·ቁ· 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org